በኢ/አ/ተ/ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን

ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ዋና ክፍል የተዘጋጀ

□□□□ □/□ □□□ □□□ (B.Th)

፳፻፲ ዓ.ም

አዲስ አበባ

ምዕራፍ አንድ

1.የነገረ ሃይማኖት መግቢያ

መግቢያ

በአንድ ወቅት በማኅበረ ቅዱሳን ከሚሰጡ ሥልጠናዎች አንዱ በሆነውና ከጠረፋማ አካባቢ ለሚመጡ ሠልጣኞች በተዘጋጀ መርሐ ግብር አንድ ሥልጠና ሰጪ ከፊት ለፊት ባለው ነጭ ሰሌዳ /white bord/ "**ነገረ ቅዱሳን**" ብሎ በትልቁ ይጽፋል የሥልጠናው ርዕስ መሆኑ ነው አሠልጣኙ ስለ ቅዱሳን ብዙ ከተናገረ በኋላ ከሠልጣኙ መሐል አንዱ እጁን ከፍ አድርጐ በማውጣት መጠየቅ እንደሚፈልግ በማሳወቁ ተፈቀደለትና እንዲህ ሲል ጠየቀ ቅዱሳን እነማን እንደሆኑ በደንብ አውቀናል እኔ ያልገባኝ ነገረና ቅዱሳንን ምን አናኛቸው አለ፡፡ እውነቱን ነው ‹ነገረ ቅዱሳንን ስንል ምን ማለታችን ነው)› ተብሎ ነበር ሥልጠናው መጀመር የነበረበት አሁንም ነገረ ሃይማኖት ስንል ነገርና ሃይማኖት ምን አገናኛቸው የሚል ጥያቄ ከመፈጠሩ በፊት ይህን ማብራራት ግድ ይላል፡፡

ትርጉም

ነገር› ስንል እኛ በቅርብ የምናውቀውን ‹ጣጣ› ሳይሆን አሳብ፣ ትንታኔ፣ መግለጫ፣ ሁኔታ ማለታችን ነው፡፡ ‹ነገር› እንደ ቅድስት ቤተክርስቲያናችን አስተምህሮ የአንድን ትምህርት መስክ የምንገልጥበት ቃል ነው፡፡ በዚህ መሠረት ነገረ ቅዱሳን ሲል ስለ ቅዱሳን የምንማርበት ሆኖ ነገረ ማርያም ሲል ደግሞ ስለ እመቤታችን ቅድስ ድንግል ማርያም አጠቃላይ ሁኔታ ክብር፣ ጸጋ፣ ምልጃ ወዘተ... የምንማርበት የትምህርት ዘርፍ ማለት ነው፡፡ በዚህም ይዘቱ ‹ነገር› የሚለው የአማርኛ ቃል Logy /ሎጂ/ ከሚለው የእንግሊዘኛ ቃል ጋር ስምም ነው፡፡

ስለዚህ ነገረ ሃይማኖት ማለታችን አጠቃላይ ስለ ሃይማኖታችን ምነነት፤ ማንን እንደምናመልክ ባለቤቱን፣ ለምን እንደምናመልክ ምክንያቱን፣ እንዴት እንደምናመለክ ሥርዓቱን በዝርዝር የምናጠናበት አንዱ የትምህርት ዘርፍ ነው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ የትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ በዋናነት ትምህርተ ሃይማኖትን ማጥናት የሚያስገኘውን ጥቅምና የሃይማኖትን፣ የፈጣሪንና የፍጥረቱን ምንነት እናጠናለን፡፡

የሚጠበቅ ብቃት /Expected Outcomes/

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲጨርሱ

- ነገረ ሃይማኖትን የማጥናት ዓላማና ጥቅምን ያብራራሉ፡፡
- የሃይማኖትና ዕምነትን ምንነት፣ልዩነትና አንድነት በሚገባ ይተነትናሉ፡፡
- የእግዚአብሔርን ሀልዎት፣ማንነትና የመገለጫ ባሕርያቱን በሚገባ ተረድተው ያስረዳሉ፡፡
- የሰውን ልጅ ጨምሮ የፍጥረታትን ምንነትና ማንነት፣የአፈጣጠራቸውን ሥርዓት፣ የተፈጠሩበትን ዓላማና ምክንያት ከነምሳሌነታቸው ጭምር አውቀው ያሳውቃሉ፡፡
- የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ምንጮችን ይለያሉ እግረ መንገዳቸውንም የሌሎች የዕምነት ተቋማትን አስተምህሮ በእነዚሁ ምንጮች ሚዛንነት ይገመግማሉ፡፡

1.2. ነገረ ሃይማኖትን የማጥናት ዓላማና ጥቅም

ውድ አንባቢያችን ሃይማኖተኛ ነኝ ብለህ(ሽ) ታስባለህ(ቢያለሽ) ስለሃይማኖትህ(ሽ) ማጥናት ማለትም መማርና ማወቅስ ትፈልጋለህ(ጊያለሽ) ከፈለግህ(ሽ) ይህ የሚያስገኘው ጥቅም ምንድነው? እስኪ ይህንን ጉዳይ ለራስዎ ከመለሱ በኋላ ወደቀጣዩ ንባብ ይለፉ፡፡

የሰው ልጅ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ ልቆና ገኖ የተፈጠረ ባለሙሉ ነፃነት ፍጥረት ነው፡፡ የሚያሳዝነው ግን ይህንን ነፃነቱንና ታላቅነቱን ጠንቀቆ ባለማወቁ ምክንያት ሲጎዳ ይኖራል፡፡ "ሰብእሰ እንዘ ክቡር ውእቱ ኢያእመረ፤ ወኮነ ከመ እንሰሳ ዘአልቦ ልብ ወተመሰሎሙ፤ ሰው አዋቂ ሲሆን እንደ አላዋቂ ሆነ አእምሮ እንደሌላቸው እንደ እንሰሳት ሆነ" እንዲል፡፡ /መዝ. 48፡12/

የሰውን ልጅ አዋቂ ያስባለችው ህያዊት ፣ ነባቢትና ለባዊት /አሳቢ፣ተናጋሪና፣ህያው፣ / የሆነችው ነፍሱ ናት፡፡ "እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወተ እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ / a living Soul/ ያለው ሆነ" /ዘፍ 2፡7/

እንግዲህ በዚህች ነፍሱ ነው ሰው ከሌሎቹ ፍጥረታት የሚልቀው። ይህቺ አዋቂና ህያው ነፍስ ስላለችውም ለምን /why / እንዴት/How/፣ መቼ /When /፣ የት / where/ ፣ ማን /who/... ወዘተ እያለ ይጠይቃል ።

ስለዚህ አንድ ሰው ነገረ ሃየማኖትን ማጥናት ያለብኝ ለምንድነው፣ ዓላማውና ጥቅሙስ ምንድነው ብሎ ቢጠይቅ ከጤነኛ አእምሮ የመነጨ ተገቢ ጥያቄ ነው የሚሆነው። በመሆኑም ለዚህ ጤነኛ ጥያቄ ቅድሰት ቤተክርስቲያናችን ምላሽ አላት ምላሹን በትህትና ሆኖ ማጥናትና መቀበል ግን ከሁሉም ክርስቲያን የሚጠበቅ ነው። በክርስትና ጉዞ ለጊዜው ያልተገለጠለን፣ የእኛ ጽናትና ብርታት እየታየ በጊዜው ጊዜ የሚገለጥልን ነገር በመኖሩ በእምነት ተቀብለን በተስፋ መጠበቅ ይኖርብናል።

ልትክደው(ጂው) የማትችለው(ቺዩው) አንድ ሃቅ አስታውስ(ሺ) አንተ(ቺ) በዚህ ሥፍራ የተገኘኽው(ሸው) ዓላማዊ ትምህርትህን(ሽን) ለማጥናት ነው። ክርስትናን ለመማር የፈቀድከው(ሸው) ደግሞ እግረ መንገድህን(ሽን) ነው። እንኳንስ በዚህ መንገድ ቀርቶ ሙሉ ጊዜያቸውን ለዚሁ ቅዱስ ዓላማ ያዋሉት ቅዱሳን ሐዋርያትም እስከ ድርገተ ጰራቅሊጦስ /የመንፈስ ቅዱስ መውረድ/ ድረስ ምስጢር ይከፈልባቸው ነበር። ለዚህም ነው ክብር ምሰጋና ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ "... የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም ግነ እርሱ የእውት መነፈስ በጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል.."። (ዮሐ16፡12) ሲል ያሰገነዘባቸው።

ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደነገረን እንዲህ ባለ አእምሮ እያሰብን የሚጎድለን ነገር መኖሩንም እየተረዳን ጎዶሎአችንንም እንዲሞላልን እየለመንን እንቆያለን ማለት ነው። "እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንደከፈለው እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ።" /ሮሜ 12፡3/

የክርስትና ሃይማኖት ትምህርት መሠረቱ በቅድሚያ የዚህ ዓለም /የሚታየውና የማይታየው/ ፈጣሪና ሠራዒ መጋቢ መኖሩን ማመን ነው። ስለዚህ የሃይማኖት ትምህርት ሁሉን የፈጠረና የፈጠረውን ዓለም በሠራዒ መጋቢነት የሚመራ አንድ አምላክ መኖሩን በመመስከር ይጀምራል። ለመመስከር ደግሞ ማየት ያልያም ማወቅ ያስፈልጋል ‹... የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን...።› እንዲል / ዮሐ.3፡11/

ለማወቅ ደግሞ መማር ግድ ነው። ይህ ሲባልም ሰባ አንድ ቋንቋ በሰከንድ መግለጥ የሚችለው የእግዚአብሔር ጥበብ ወይም ተዓምር እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው።/ግ.ሐዋ 2፡14/ ኢትዮጵያውንም በብሂላቸው "ካልተማሩ አያውቁ ካላወቁ አይጸድቁ" የሚሉት የዕውቀትን ጥቅም ለማጉላት ነው።

ሌላውና አስፈላጊው ትምህርተ ሃይማኖትን የመማር ጥቅም የክርስትና ጉዞአችንን ቅደም ተከተል ለማስተካከል ስለሚረዳን ነው።

ክርስትና በስሜት የምንከተለው እምነት አይደለም ቅደም ተከተሎች አሉት። እነርሱም ማመን ፣መታመንና መመስከር ናቸው›። አንድ ክርስቲያን ወደ አምልኮትና አገልግሎት ከመግባቱ በፊት በእምነት እግዚአብሔርን ማወቅ፣ ይኖርበታል። ይኽ ደግሞ ቀዳሚውና የመጀመሪያው መስመር ነው።

አንዳንድ ሰው እግዚአብሔርን የሚያውቀው በከፊል ነው ። ይህም ማለት ሰጪነቱን እንጂ ነሺነቱን አያውቅም ፤አዳኝነቱን እንጂ ገዳይነቱን/በሞት የሚጠራ መሆኑን/ አያውቅም፣ ምሕረቱን እንጂ መዓቱን፣ትዕግሥቱን እንጂ ቁጣውን፣ ርኅራኄውን እንጂ ጭካኔውን አያውቅም። እስኪ እነዚህን ጥቀሶች ተመልከት(ቺ)፡-

- “እግዚአብሔር ይገድላል ያድናልም፤ ወደ ሲዖል ያወርዳል ያወጣል”(1ኛሳሙ 2፡6)፣
- “... እኔ ሠርቻለሁ እኔም አነሣለሁ፤ እኔ እሸከማለሁ እኔም አድናለሁ..”(ኢሳ 46፡4)
- “ ኑ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ እርሱ ሰብሮናልና እርሱም ይፈውሰናል እርሱ መትቶናል እርሱም ይጠግነናል” (ት.ሆሴ 6፡1)

እስኪ አስተውል(ዪ) በእነዚህ ጥቅሶች ብቻ እግዚአብሔር እንደሚገድል፣ እንደሚያድን፣ እንደሚያወርድና እንደሚያወጣ፣ እንደሚያነሣና እንደሚሸከም፣ እንደሚሰብርና እንደሚጠግን ትመለከታለህን(ቺያለሽን)? ታዲያ እግዚአብሔር ምንድነው? ጨካኝ ነው ሩኅሩኅ?፣ ፍትሐዊ ነው አድሎአዊ?፣.....እስኪ የምታስበውን(ቢውን) ሁሉ በወረቀት ላይ አስፍረው(ሪው)። በጽሑፍ የሰፈረው አሳብህ ምንም ይሁን ምን እነዚህ ሁለቱ ጥቅሶች ብቻ እንኳን ሊያርመልህ(ሽ) ይችላሉ።

- “ምድርና ሰማይን የምገዛ መወደድንና ክብርንም የምሰጥ የማድንና የምገድልም እግዚአብሔር እኔ እንደሆንኩ የዚያን ጊዜ ያውቁኛል” (1ኛ መቃብያን 34፡10)

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ፈጣሪዋን በምሉዕ ስልጣኑ ስለምታውቀው በጸሎቷ እንዲህ ነበር የገለጸችው "... ወዘረዎመ፡ ለእለ ያዐብዩ ኀሊና ልቦመ፡ ወነሠቶመ፡ ለኃያላን እመናብርቲሆመ፡ አዕበዮመ፡ ለትሑታን ወአጽገቦመ፡ እምበረከቱ ለርኁባን ወፈነዎመ፡ እራቆመ፡ ለብዑላን..። ትዕቢተኞችን በልባቸው አሳብ በትኗል። ገዥዎችን ከዙፋናቸው አዋርዷል ትሑታንንም ከፍ ከፍ አድርጓል። የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቧል። ባለጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል።"(ሉቃ 1፡51-53)

እግዚአብሔር ያድናል ብሎ ብቻ የሚያምን ሰው ይገድላል ሲባል ላያምንና ሲገድልም(ፍጥረቱን በሞት ሲጠራ) ሲያይ ሊማረር ይችላል። ያድናል ይገድላልም ብሎ የሚያምን ግን እንኳንስ ሊጠራጠርና ሊያማርር ይቅርና እንደ ቅዱስ ጳውሎስ እባክህን በሞት ውሰደኝ ብሎ እስከመናፈቅ ሁሉ ሊደርስ ይችላል።

"በእነዚህ በሁለቱ እጨነቃለሁ ልሔድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻለ ነውና..."። እንዲል (ፊሊ 1፡23)

ልክ እንደዚሁ ሁሉ እግዚአብሔር ሰጪ ነው ብሎ ብቻ የሚያምን ሰው ሲነሳ /ሲወስድ/ ቢያይ ሊያማርርና ሊክድ ይችላል። እግዚአብሔር ሰጪም ነሺም ነው ብሎ የሚያምንና የሚታመን ግን እንደ ጻድቁ ኢዮብ "ራቁቴን ከእናቴ ማኅፀን ወጥቻለሁ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሳ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን" ይላል /መጽ ኢዮ 1፥21/ ቆይቶም በእግዚአብሔር በረከት ይትረፈረፋል።

ይህ እንግዲህ እግዚአብሔርን የማውቅ ውጤት ከሆነ እግዚአብሔርን ለማወቅ ደግሞ ትምህርተ ሃይማኖትን ከመማር ውጪ ሌላ አማራጭ የለም። ውድ አንባቢያችን ትምህርተ ሃይማኖትን የመማር ጥቅም በግልጽ ሲታይ አስተዋልክን(ሽን)?

ሁለተኛው መስመር ደግሞ እግዚአብሔርን መውደድ ነው በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን እንድንወድ ታዘናል እንዲያውም ይህቺ ትዕዛዝ ፊተኛ ትዕዛዝ ናት "... ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህቺ ናት" ተብሎ ተቀምጧል። /ማቴ 22፥37-38/

በመጀመሪያውና ቀዳሚ ተብሎ በተቀመጠው መስመር እንደተገለጸው እግዚአብሔርን በሚገባ የሚያውቀው ሰው እግዚአብሔርን ከመውደድ ሰስቶ የሚተርፈው ጊዜ፣ የሚቀረው

ልቡና፣የሚቆጥበው ጉልበት አይኖረውም። ይወደዋል። የሚወደው ደግሞ የሚፈልጋቸው ነገሮች እንዲደረጉለትና ስለተደረጉለት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር በመሆኑ ብቻ ነው። የዚህ ውለታን መሠረት ያላደረገ ፍቅር ጀማሪ ደግሞ እኛ አይደለንም። እሱ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ነው። ‹እኔ መረጥኋችሁ እናንተ አልመረጣችሁኝም›። እንዳለው / ዮሐ 15፥16/

ስለዚህ እሱን በመውደዳችን አትራፊዎቹ እኛ ነን። ይህንን በመጀመሪያ እግዚአብሔር ማን መሆኑን ባወቅን ጊዜ ተረድተናል። በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕለት በሚጸለየው በሐመስ ውዳሴ ማርያም ላይ አባታችን ቅዱስ ኤፍሬም ሲናገር "ሰማዕታት የዚህችን ዓለም ጣዕም በእውነት ናቁ ደማቸውንም ስለ እግዚአብሔር አፈሰሱ ስለ መንግሥተ ሰማያትም መራራ ሞትን ታገሱ" ያለላቸው ሰማዕታትን ለዚህ ያበቃቸው ከሁሉ የሚበልጠውን እግዚአብሔርን እና የእሱ የሆነውን አስቀድመው በማወቃቸውን በመውደዳቸው ጭምር ነው። ሐዋርያትም ሲገረፉ ደስ ያላቸው እግዚአብሔርን በሚገባ ስላወቁትና ስለወደዱት ነው። /ግ.ሐዋ 5፡41/

ሦስተኛውና የመጨረሻው መስመር እግዚአብሔርን ማምለክ ወይም ማገልገል ነው አንድ ሰው ከላይ ባስቀመጥነው መሠረት እግዚአብሔርን ካወቀውና ከወደደው እንዴት ነው የማያመልከውና የማያገለግለው?እንዴትስ ነው ክርስትናን ጀምሮ ሊያቋርጥ የሚችለው?ብዙዎች ግን እግዚአብሔርን በመጠኑ እንኳን ሳያውቁት እንወደዋለን ብለው ፍቅራቸውን በከንፈራቸው ያሰማሉ። ሳያውቁትና ሳይወዱት እናመልከዋለን እናገለግለዋለንም ብለው ጎንበስ ቀና ይላሉ።በመሆኑም ጉዞአቸው ሁሉ የህልም ሩጫ እየሆነባቸው እሩቅ እያሰቡ ቅርብ ያድራሉ። ቆይተውም የነበርኩበትን ትረካ ያዘወትራሉ። ማለትም እኔ እኮ ክርስትናውን ነበርኩበት፣ እንትን የተባለውን ገዳም አውቀዋለሁ፣ እንትና የተባለው ሰባኪም ጓደኛዬ ነበረ አብረን ፎቶ ተነስተናል፣.....ወዘተ። ይላሉ። ይህ ሁሉ ችግር የሚመጣው ደግሞ ከላይ እንዳስቀነጥነው የክርስትና ጉዞ ቅደምተከተል ካለመስተካከሉ የተነሳ ነው። ይህ የተስተካከለ ጉዞ የሚመጣው ደግሞ ትምህርተ ሃይማኖትን በሚገባ በመማር ነው። ስለዚህ መማሩ እጅግ በጣም ወሳኝና አስፈላጊ ነው።

አሁን ራስህን(ሽ) ጠይቅ(ቂ) በእርግጥ የክርስትና ጉዞህ(ሽ) አልተዘበራረቀም? ይህንን በምን አውቀዋለው? አትበል(ዪ) እንዲህ ብለህ(ሽ) ራስህን(ሽን) ጠይቀው(ቂው)

በእርግጥ እኔ እግዚአብሔርን አውቀዋለሁ?፣ እግዚአብሔር ማነው) በእርግጥስ እወደዋለሁ)፣ ደግሞስ እግዚአብሔርን እያመለኩት ወይ እያገለገልኩት ነውን) ከየትኛው ነው የጀመርኩት?፣ወይስ ከየትኛው ልጀምር?

እግዚአብሔርን እወደዋለሁ ብለህ(ሽ) ታምንን(ኚ) ይሆናል።አሁን እግዚአብሔር ትወደኛለህን? ብሎ ቢጠይቅህ(ሽ) መልስህ(ሽ) ምንድነው? መልስህ(ሽ)?እዚህ ላይ ምላሹ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ የከንፈር ብቻ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በአንድ ወቅት ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሁለት ዓይነት ምላሽ የሰጠበት ሁለት ዓይነት ሰው የሆነበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። ነገሩ እንዲህ ነው; ጌታችንና መድኃኒታች ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ትተውት እንደሚሸሹ ሲነገራቸው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ነበር ያለው "ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ ከቶ አልሰናከልም ... ከአንተ ጋር መሞት እንኳ የሚያስፈልገኝ ቢሆን ከቶ አልክድህም።" (ማቴ 26፡33)

የሚያሳዝነው ግን ዶሮ ሳይጮኽ(ያቺ ሌሊቱ ሳይነጋ) ሦስት ጊዜ መካዱ ብቻ አይደለም አካካዱ እንጂ "ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ሊረግምና ሊምል ጀመረ" ይለናል። የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 26፡14

አየህ(ሽ) አይደል ቅዱስ ጴጥሮስ በዚያች ቀውጢ ቀን ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ማለትን በፍርሃት ምክንያት ተጠይፎ "ሰውየውን" ብሎ በመጥራት ሲክደው። በዕውነት እጅግ በጣም ያሳዝናል። ይህ ክስተት የሚያሳየን እግዚአብሔርን ማወቅ መሠረቱ ያልሆነለት ክርትና አደጋው ከፍተኛ መሆኑን ነው። ትምህርተ ይማኖትን መማር ደግሞ ከዚህ አደጋ መውጫ ብቸኛ መንገድ ነው።

እስኪ ሌላ አንድ እውነተኛ ታሪክ ልጨምርልህ(ሽ) በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ማለትም በዘመነ ሰማዕታት አንዲት እንዳንተ(ቺ) በወጣትነት የዕድሜ ክፍል ላይ የምትኝ እናቷ በመሞቷ ምክንያት አባቷ ከአምስት ወንዶች መኽል ለብቻው ያሳደጋት ጴርጴትዋ የምትባል ክርስቲያን ተይዛ ብዙ ከተሰቃየች በኋላ ወደ መገደያ ሥፍራ ተወሰደች በዚያም ኢየሱስ ክርስቶስን በመካድና በመራገም ማስተባበያ እንድትሰጥ ታስቦ አደባባይ ወጣች።

ሕዝቡ ተጨናንቆ ተገኝቷል፡ በግራ በቀኝ ወታደሮች አሉ ከፊት ለፊት የዚህች ሴት ሽማግሌ አባቷ ተቀምጧል አዲስ ሙሽራ እንደመሆኗ አያት እንድታደርገው ተስፋውን ጥሎባት ሳለ ነው ይህ ሁኔታ የተፈጠረው፡፡

ንጉሡ ዲዮቅልጥያኖስ አባቷን "ሒድና የምትሰማህ ከሆነ አባብለህ የልጅህን ነፍስ አትርፍ" ብሎ ላከው አባት ተንደርድሮ ወደልጅቱ ተጠጋና "ልጄ አባክሽን ስለ እኔ ስለአባትሽ ብለሽ፤ይህም ባይሆን በሆድሽ ስለያዝሽው ጽነስ /ነፍሰጡር ነበረች/ ብለሽ ይህንን መከራ በጥበብ እለፊ ዛሬ በአንደበትሽ ካጂና በልብሽ እመኚ" ሲል ወተወታት፡፡ እስኪ ራስህን(ሽን) በዚህች ልጅ ጫማ አስገባና(ቢና) አስብ(ቢ) አንተ(ቺ) ብትሆን(ኚ) ምን የምታደርግ(ጊ) ይመስልሃል(ሻል)?

ልጅቱ ተጨነቀች ወጣት ነች በዚያ ላይ ነፍሰጡር፤ አጠገቧ ምድራዊ አባቷ፣ቀና ስትል ደግሞ ሰማያዊ አባቷ፤ ሁለቱንም አየቻቸው...እንዴት ያስጨንቃል? ያቺ ሴት ግን አባቷን ያንን የሸክላ ዕቃ አምጣልኝ አለችው ከፊት ለፊቷ የአበባ ማስቀመጫ የሸክላ ዕቃ ነበር፡፡ አባት በፍጥነት አመጣላት፡፡ "ይኼ ምንድነው?" ስትል አባቷን ጠየቀችው "ምነው ልጄ ምን ነካሽ ይኼማ ሸክላ እኮ ነው" አላት ጥያቄዋን አጣጥሎ፡፡ እሷም ቀጠለች "ይኸውልህ አባቴ አንተ ይህንን ዕቃ የጠራኸው በስሙ ነው ሸክላ ስለሆነ ሸክላ አልከው፡፡ እኔም የጨነቀኝ ጉዳይ ይኼ ነው፡፡ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው ከቶም ቢሆን ሌላ ስም ልሰጠው አልችልም" አለችና በዛ ሁሉ ሕዝብ ፊት ሳትፈራ ስለ እግዚብሔር እግዚብሔርነት መሰከረች፡፡

ንጉሡ ተቆጥቶ አባቷን ካስገፈተረ በኋላ እሷን ወደ አናብስት ጉድጓድ አስወረወራት ሕፃኑ ተወለደ እሷ ሞተች... ቅዱስ ጴጥሮስ ግን ክርስቶስን "ሰውየው" ብሎ ጠራው አላውቀውም ብሎም ካደው በኋላ ቢመለስም፡፡ በዚህች ቅድስት ተጋድሎ ውስጥ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ አርጋኖን በተባለ የውዳሴ ድርሰቱ "መታመን ይጀምራል ሃይማኖት ይፈጽማል" ሲል የተናገረው ቃል አማናዊ እንደሆነ እናይበታለን፡፡ ይህች ወጣት ያመነችውን አውቃ እና ወዳ ለአወቀችውና ለወደደችውም ታምና በሰማዕትነት እንዳገለገለች ትመለከታለህን(ቺያለሽን)? ማገልገል ማለት ይኸው ነው፡፡ ማመን፣መታመንና መመስከር፡፡ እንዲህ መሆን አልናፈቀህም(ሽም)?

የዚህ የትምህርተ ሃይማኖት ጥናት ዋነኛ ዓላማውም ሰው የሚያመልክውንና የሚያገለግለውን አምላክ እንዲያውቀው፣ የሚያውቀውንም እንዲወድ፣ የሚወደውንም እንዲያገለግለው ማስቻል /ማብቃት/ነው፡፡ ጥቅሙም ከላይ ለማስቀመጥ እንደተሞከረው አንድን ክርስቲያን ሦስቱ መስመሮች ላይ ማለትም እግዚአብሔርን ማወቅ፣መውደድና ማምለክ(ማገልገል)

የሚሉት ላይ አስቀምጦ ጉዞዉን ማመቻቸት ነው። ይህ ሲሆን ደግሞ ማንን እንደሚያመልክና እንደሚያገለግል ባለቤቱ፤ ለምን እንደሚያገለግል ምክንያቱ ስለሚገባው በሃይማኖቱ እስከ መጨረሻው ጸንቶ ከሚድኑት ወገን ይሆናል እንጂ በግብጽ በረሃ ወድቀው እንደቀሩት የምድረ ርስት ተጓጉሾች አይሆንም ማለት ነው። “እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል”። ተብሏልና ማቴ 24፡13

1.3. ሃይማኖት ምንድን ነው

ሃይማኖት ምንድነው የሚለውን ጥቅል አሳብ ከማየት በፊት የሚቀድም ነገር አለ ሃይማኖት ማለት የቃሉ ፍቺ ምን ማለት ነው)

ብዙ ጊዜ ሃይማኖትና እምነት የሚሉት ቃላቶች በአንድም በሁለትም ሲተረጎሙና ሲተነተኑ ይሰተዋላል ይህንን ነገር አስበኸው/ሸው/ ታውቃለህ/ሽ/ እስኪ ከራስህ /ሽ/ ዕውቀት ተነሳና/ሺና/ የሁለቱን ቃላት ልዩነትና አነድነት አብራ/ሪ/

ሃይማኖትና እምነት

መጽሐፍ ቅዱስ ሁለቱን ቃላት በተገቢው ቦታ በሚገባ ተጠቅሞባቸዋል ይህንን በጥንቃቄ ማየትና መመርመር ይገባል በዚሁ መሠረት ሃይማኖት የሚለው ቃል ብቻ ቃል በቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በሐዲስ ኪዳን ብቻ 19 ጊዜ ተጠቅሷል። እምነት የሚለው ቃል ደግሞ በብሉይ ኪዳን 7 ጊዜ በሐዲስ ኪዳን 165 ጊዜ በድምሩ 172 ጊዜ ተጠቅሶ እናገኘዋለን።

ከዚህ ቀጥለን የሁለቱን አንድነትና ልዩነት በዝርዝር እንመለከታለን።

ሃይማኖት

ሃይማኖት የሚለውን ቃል ስታስታውስ(ሽ) በፊትህ(ሽ) ድቅን የሚለው ሕግና ሥርዓት ያለው፣ የወል /የጋራ/ የሆነ፣ በሥሩ ይብዛም ይነስም ተከታዮች ያሉት ሰፊ ማዕቀፍ /ተቋም/ ከሆነ ጥሩ አስታውሰሀል(ሻል)። እስኪ ይህንን ጉዳይ ወደ ራስህ(ሽ) አስጠጋው(ጊው) ምን ይታይሃል? መጽሐፍ ቅዱስን ማዕከል ያደረገ የራሷ ዶግማና ቀኖና ያላት ንጽሐት ቅድስትና አርቶዶክሳዊት /ሃይማኖት ርትዕት/ ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ከታየችህ(ሽ) ትክክለኛ ዕይታ ነው።

ለምሳሌ ሐዋርያው ይሁዳ ‹በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚወስደውን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ› በማለት በጋራ የምንከተላት ሃይማኖት የምታስተምረውንና የምትሰብከውን የክርስቶስን ምሕረትና የዘለዓለም ሕይወት ይነግረናል / ይሁ. ቁ.20 / በነገራችን ላይ በያዝከው(ሽው) የተቀደሰ ሃይማኖት ራስህን(ሽ) ለማነጽ ምን ያህል እየተጋህ(ሽ)ነው? ምክንያቱም ይህ ቃለ እግዚአብሔር የሚነግረን ስለሃይማኖት ምንነት ብቻ ሳይሆን በዚህ ሃይማኖት ታንጸ የመኖሮን አስፈላጊነትም ጭምር ስለሆነ ነው።

በሌላ ቦታም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹... እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተሰቦች መልካም እናድርግ› በማለት የወል /የጋራ/ በሆነው ሃይማኖት ውስጥ ያለነው ሰዎች ሁሉ የሃይማኖት ቤተሰቦች መሆናችንን ጠቅሶ እገሌ የምግባር ድኃ ነው፣ እገሌ ክፉ ነው፣ እገሌ ደግ ነው፤ እገሌ ቀይነው፣ እገሌ ጥቁር ነው፣ እገሌ ከዚህ ጎሳ ነው እገሌ ከዚያ ጎሳ ነው ሳንል ለሃይማኖት ቤተሰብ የጋራ ሃይማኖት ባለቤት በመሆኑ ብቻ መልካም ነገር አብልጠን እንድናደርግለት ያዘናል። / ገላ 6፡10/

እምነት

እምነት የሚለው ቃል በቀጥታ የሚያመለክተን ከተቋም እንዲሁም ከወል /ከጋራ/ ከሆነው እሳቤ ይልቅ የእያንዳንዳችንን ማለትም በአንድ ሃይማኖት ሥር ያለነውን የማመንና የመታን ጉዳይ ነው። ብዙ ሰዎች በአንድ ሃይማኖት ጥላ ሥር ቢሆኑም በተለያየ የእምነት ደረጃ ላይ ሊገኙ እንደሚችሉ ታውቃለህ(ሽን)? የቅዱሳንን ማዕረግ በሚያስረዳው ክፍለ ትምህርት እነደተቀመጠው በአንድ ሃይማኖት ጥላ ሥር ያሉት ቅዱሳን ልዩ ልዩ መዓርግና ክብር አላቸው ዳሩ ግን አንዲት ሃይማኖት የሁሉም ናት ይህ ክብራቸው የሚወሰነው እንደየ እምነታቸው ልክና መጠን ነው። “በክብር አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይለያልና”። እንደተባለው /1ኛ ቆሮ 15፡41/

እስኪ መጸሐፍ ቅዱስ እምነትን እንዴት እንደገለጠው እንይ በአንድ ወቅት ክብር ምሰጋና ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን እንዲህ ብሏቸው ነበር "... እናንተ እምነት የጎደላችሁ ስለ ምን ትፈራላችሁ..." ሐዋርያትም እምነት የጎደላችሁ የምትለዋን ግሳፄ በተለያየ ጊዜ ሰምተዋት ስለበረ አንድ ቀን እንዲህ ሲሉ አምላካችንን ጠየቁት “..... እምነት ጨምርልን....” /ሉቃ 17፡5/ በአንድ ሃይማኖት ጥላ ሥር ያሉት ሐዋርያት ምርጫው ያልተጠናቀቀበት ጊዜ ቢሆንም አንዱን አግዚአብሔር እየተከተሉና በአንድነት እየተጓዙ

ነው ያሉት፡፡ እምነት ጨምርልን ማለታቸው ከላይ የሃይማኖትን ትርጓሜ ባስቀመጥንበት አንጻር ሌላ እግዚአብሔር ሌላ ሕግ ሌላ ሥርዓት ያስፈልገናል ሃይማኖት ጨምርልን በርከት ቢልልን ጥሩ ነው አማራጭ ይሆነናል ማለታቸው አይደለም፡፡ የሐዋርያቱ ጥያቄ በማር. ወንጌል 9፡24 ላይ እንደተጠቀሰው “አምናለሁ አለማመኔን እርዳው” ዓይነት ልመና ነው፡፡ ሌላ ኃይለ ቃል እንጨምር “ በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ” ። /1ኛ ጢሞ 5፥8/ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ኃይለ ቃል ሁላችን በጋራ የምንከተላት የምንኖርባት ሃይማኖት ሕግ /ዶግማ/ ሥርዓት /ቀኖና/ እንዳለን ካስታወሰ በኋላ ምንም እንኳን በዚህች አንዲት ሃይማኖት ጥላ ሥር ብትኖሩም ስላላችሁ ብቻ የዘለዓለምን ሕይወት አትወርሱምና እያንዳንዳችሁ ራሳችሁን መርምሩ፤ ማለትም ፈትኑ፣ ጠይቁ፣ ንስሐ ግቡ፣ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ሥራ ተመለሱ፣ ምግባር ትሩፋትን ጠብቁ አጽኑ፡፡ የሚለውን ግላዊ መልእክት ነው የሚያስተላልፍልን፡፡ ስለዚህ እምነት የሚለው ቃል ከእያንዳንዳችን የማመንና የመታመን ሁኔታ ጋር ይገናኛል ያልነው ለዚህ ነው፡፡

ይህ ሁሉ ይሁን እንጂ ሃይማኖትና እምነት ሁለት ሲሆኑ አንድ አንድ ሲሆኑ ሁለት የሆኑ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ በተለይም የግዕዙን መነሻ ቃል ወስደን ስናያቸው ልዩነታቸው ይጠባል አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በአማርኛ መዝገበ ቃላት መጽሐፋቸው ሃይማኖት በቁሙ ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ ጽኑ ተስፋ፣ የአምልኮ ባሕል፣ በልብ ረቂቅ ሐሳብ የሚሳል ማለት ነው፡፡ ሲሉት እምነትን ደግሞ በቁሙ ሃይማኖት፣ ማመን፣ መታመን፣ አስተማማኝ፣ እሙንነት ብለው ይፈቱታል፡፡ ለዚህም ነው አብዛኛው የቤተክርስቲያናችን ሊቃውንት ልዩነት እንደሌላቸው የሚያስተምሩት “ሃይማኖት ወይም እምነት የሚሉት ቃላት በንባብ እንጂ በፍቺው ልዩነት የላቸውም በምሥጢሩ ግን በሁለት ይከፈላል ይኸውም ማመን፣ መታመን ተብሎ ነው”። ሊቀ ትጉሃን ኃ/ጊዮርጊስ ዳኜ /መሠረተ ሃይማኖት ገጽ 20፤2004/

የቃላት ፍቺውን በተመለከተ ይህን ያህል ካልን ሃይማኖት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ መሠታዊ የሆኑ ትንታኔዎችን እናያለን ሃይማኖት /እምነትን/ በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል ይኸውም አንዱ ክፍል ማመን ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ መታን ማለት ነው፡፡

ማመን፡- ማለት በዓይነ ሥጋ አይቶ ፣ በዕዝነ ሥጋ/ጆሮ/ ሰምቶ፣ በልብ አስቦ በአጠቃላይ በስሜት ሕዋሳትም ቢሆን አድምጦና ዳሶ ሊመረምሩት የማይቻለውን በርቀት /ሩቅ በመሆን/ እና በርቀት /በረቂቅነት/ ያለውን ይሆናል፣ ይደረጋል ብሎ መቀበልና እግዚብሔርን አለ፣ ይኖራል ሁሉን ያዥ ሁሉን ገዥ ነው ብሎ በልብ በረቂቅ መሳልና ማሰብ፤ ሐሳብን በማወቅ ማረጋገጥ፣

መፍቀድ መውደድ መመካት ተስፋ ማድረግ ማለት ነው / ትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ 2002 /ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ ፤ /መሠረተ ሃይማኖት/2004 ሊ/ት/ኃ/ጊዮርጊስ ዳኜ /

መታመን፡- ማለት ደግሞ በልብ በረቂቅ አሳብ ያመኑትን በአንደበት መመስከር፣ መናገር፣ ወዶና ፈቅዶ በደስታ መቀደስ፣ ማመስገን፣ በግብር መግለጽ፣ ማምለክ፣ መስገድ መገዛት ፣ መገበር፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ንስሐ ኃጥኡን ጻድቅ፣ዘማዊውን ድንግል ታደርጋለች ብሎ ቢያምንም ንስሐ ገብቶ መታመኑን መግለጽ አለበት፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ሃይማኖትን በሚከተሉት ነጥቦች መግለጽ እንችላለን፡-

1ኛ.መንገድ /ፍኖት/ ነው

ሃይማኖት ከጥንት ከመጀመሪያው የሰውና የልዑለ ባሕርይ የህያው እግዚአብሔር ግንኙነት ነው፡፡ የሰው ልጅ ከብሮና ልቆ ከተፈጠረና አድርግ አታድርግ ከሚለው አምላካዊ ትእዛዝ ጋር በሕይወት ተጠብቆ እንዲኖርባት በተሰጠችው ገነት ሳለ አታድርግ የሚለውን ትእዛዝ ጥሶ እምነቱን ሲያጎድል እርቃኑን የሚሸፍንበት እንኳ በማጣቱ ከእግዚአብሔር ፊት በሸሸ ጊዜ እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ስለሆነ እንደወጣህ እራስህ ግባ፤ እንደገባሃት ራስህ ተወጣት ብሎ የሰውን ልጅ በሜዳ ሳይተወው አዳምን ጠርቶ ወዴት ነህ አለው /ዘፍ 3፡9/

ስለዚህ በቅድስት ቤተክርስቲያናችን አስተምህሮ በመጀመሪያ በመፍጠርና ትእዛዝን በመስጠት ሁለተኛም ከጠፋበት በመፈለግ የሠራዊት ጌታ ልዑል እግዚአብሔር ለሰው ያሰማው ድምጽና ወደ ሰው ያደረገው ጉዞ ነው፡፡ ዛሬም ቢሆን በይማኖታችን ያለው ይኸው ነው፡፡

በመሆኑም ሃይማኖት ፍኖተ እግዚአብሔር /የእግዚአብሔር መንገድ/ ይባላል፡፡ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እግዚአብሔርም ከሰው ጋር የሚገናኙበት በመሆ የክርስትና ሃይማኖት የሚሰብከው የአምላክን መምጣትና መገለጥ ነው፡፡ አምላካችን ወደዚህ ዓለም የመጣው የጠፋውን ሰው ለመፈለግ ነው፡፡ ያኔ የመጀመሪያው ሰው በተሸሸገ ጊዜ "በገነት ድምጽህን ሰማሁ ራቁቴንም ስለሆንክ ፈራሁ ተሸሸግሁም" ማለቱን አስታውስ(ሺ)፡፡ /ዘፍ.3፡10/

"ሃይማኖት ማለት አምነህ የምትሔድበት መንገድ፤ ሔደህም በእርግጥ የምትገባባት አገር ወይም ሕያው መኖሪያ ማለት ነው" (ኮኩሐ ሃይማኖት ገጽ 113)

ልዑል እግዚአብሔር አዳምን ወዴት ነህ ብሎ ድምጹን እያሰማ እንደፈለገው በሐዲስ ኪዳንም በሥጋ ማርያም ተገልጦ ያደረገውን አምላካዊ ጉዞ በመፈጸሙ፣ ኋላም ዓለምን ለማሳለፍና ለመጨረሻ ፍርድ በመምጣቱ ሃይማኖት ፍኖተ እግዚአብሔር ቢባል ትክክለኛና ቀጥተኛ ትርጉም ነው፡፡ ይህ ፍኖተ እግዚአብሔር አንድ ስለሆነ ሃይማኖት አንዲት ናት የምንለውም ለዚህ ነው "አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት" /ኤፌ. 4፡5/

2ኛ.የተሰጠ ነው

ሃይማኖትን ማንም ሰው ተመራምሮ ተፈላስፎ ያገኘውና የሠራው ለዓለምም ያስተዋወቀው አይደለም ምክንያቱም ሃይማኖት መገለጥ ስለሆነ ይህንንም መገለጥ ያገኘነው ከባለቤቱ ከልዑል እግዚአብሔር በመሆኑ የእኛ ድርሻ ስለሌለበት የተሰጠ ያሰኘዋል ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳ በመለእክቱ " ለቅዱስን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኳችሁ እጽፍላማችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ" ያለው /ይሁዳ ቁ.3/ በዚህ መልእክትም ሃይማኖት የተሰጠች መሆኗን ብቻ ሳይሆን አንዲት መሆኗንም ነው ያስቀመጠው።

3ኛ.የሚቀበሉት ነው

የተሰጠ ከሆነ መቀበል ግድ ነው የሚቀበሉት ስንል ግን በእምነት የሚበሉት ማለታችን ነው እንጂ ባለን የአቅምና የአእምሮ ውሱንነት መርምረን አረጋግጠን የምንቀበለው ማለታችን አይደለም። እምነት ከስሜት በላይ ነው ስሜትን በሕዋሳቶቻችን ልናረጋግጠው እንችላለን። እግዚአብሔር ደግሞ መንፈስ ነው ሥራዎቹ ሁሉ መንፈሳዊ ሥራዎች /ተሠርተው የሚገኙ/ ናቸው /ዮሐ. 4፡24/ መንፈስን ደግሞ በስሜት ማለትም ቀምሰን አሽትተን፣ ዳሰን፣ ሰምተንና ዐይተን ልንረዳ አንችልም። ስለዚህ ያለን ምርጫ ዝም ብለን መቀበል ነው። ሌላው ጉዳይ ለእኛ አእምሮ ወሰን አለው እግዚአብሔር ግን ወሰን የለውም ስለዚህ በዚህ ወሰን ባለው አእምሮአችን ወሰን የሌለውን እግዚብሔርንና ወሰን የሌለው ጥበቡን መመርመር ስለማይቻል ያለው ብቸኛ አማራጭ ዝም ብሎ መቀበል ነው፡1

እስኪ አንድ እውነተኛ ታሪክ እናቅርብ ሰውየው ዶ/ር በላይ አበጋዝ ይባላሉ የሕፃናት የልብ ስፔሻልስት ናቸው። እኚህ ሰው በይበልጠ የሚታወቁት በኢትዮጵያችን ለሕፃናት የልብ ሕመማን ባደረጉት በጎ ተግባርና ባስገነቡት የሕፃናት የልብ ሕክምና ማዕከል ነው። እኚህ በጎ አድራጊ በአንድ ወቅት በሰጡት ቃለ ምልልስ / Interview / በእግዚአብሔር መኖር ያምናሉ) ተብለው ሲጠየቁ ‹ አዎን ማን አለኝ›› ካሉ በኋላ ‹ ማንም ስለሌለዎት ነው ወይስ የእርሱ በእርግጥም መኖር ነው እንዲያምኑ ያደረገዎት) ተብለው ሲጠየቁ ‹እግዚአብሔር አለ። በእግዚአብሔር አምናለሁ። ለዚህ ደግሞ ምንም ተጨማሪ ማስረጃ አያስፈልገኝም› ነበር ያሉት ሌላም ጥያቄ ተጠይቀው ነበር ዶክተሩ "ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር መኖር ማሳያ ሊሆን ይችላል ይበልጠ ግን ምን ሲገጥምዎት ነው የእግዚአብሔርን መኖር የሚያረጋግጡት" ተብለው በተጠየቁ ጊዜ የመለሱለት የሚከተለውን ነበር "እግዚአብሔር አለ። በእርግጥ አለ። የእግዚአብሔርን መኖር

ማመን እንጂ ማረጋገጥ አያስፈልግኝም። ሎጂክ አያስፈልግውም፤ በጭፍኔ / Blindly / ነው ማመን የምፈልገው" ነበር ያሉት።

በጣም የሚገርም ነው እኚ ሰው እምነታቸው ይህን ያህል ያኮራቸው ምን ቢረግላቸው ይሆን እንዴትስ ነው እዚህ ትውክልት(መመካት፣መታመን) ላይ የደረሱት? እሳቸው ብዙ ነገር ሊኖራቸው ይችላል በሕይወታቸው የተደረገላቸውን አንድ ታላቅ ነገር ግን መደበቅ አልቻሉም። ጠያቂው እንዲህ አናሂቸው ነበር "እግዚአብሔር ረድቶዎታል)" ሲል ጠይቋቸው "እግዚአብሔር ይሰማኛል ይረዳኛልም"። በማለት የኑሮአቸውን ስኬት ካስቀመጡ በኋላ አንድ አስደናቂ ነገር /ምስክርነት/ ተናገሩ።

ዶክተሩ በ1999 ዓ.ም አካባቢ ታመው ለአንድ ወር እራሳቸውን ስተው ነበር። እሳቸው በታመሙበት የአእምሮ ውስጥ ህመም አሜሪካን ውስጥ በተጠና ጥናት አንደ ሰው በሽታው በጀመረው በ3 ሰዓት ውስጥ ቀዶ ጥገና ካልተደረገለት የመሞት ዕድሉ ያላቸው 80 በመቶ እንደሆኑ ቢታወቅም /ጥናቱ ቢያጋግጥም/ ዶ/ሩ በታመሙ በ11ኛ ቀናቸው ነበር ወደ ደቡብ አፍሪካ ለሕክምና የሔዱት።

የሚያስገርመው ይህ ብቻ አይደለም። እንደታመሙ ራሳቸውን የሳቱት ዶክተሩ ረቡዕ ዕለት ታመው /ራሳቸውን ስተው/ ሐሙስ ዕለት እዚህ አዲስ አበባ በቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል ተኝተው ሳለ ሲሰተር ሰላም የተባለችውን የሥራ ባልደረባቸውን አስጠርተው ጉዳያቸውን የያዙላቸውን ሕሙማን ፋይል አስቀርበው ሲያወሩ ነበረ። ይህንን ግን እሳቸው አያውቁትም የተነገራቸውም ከነቁ በኋላ ነበር ራሳቸውን እንደሳቱ በ11ኛው ቀን ደቡብ አፍሪካ ለሕክምና ሲሔዱም እዛ ላሉት ሐኪሞች እንዴት እንደሚያክሟቸው ዝርዝር መመሪያና የባለሙያ ምክር ሲሰጡም አያውቁም፤ በኋላ ተነገራቸው እንጂ ይህ ብቻም አይደለም ደቡብ አፍሪካ እያሉ የሕፃናቱ የልብ ሕክምና ማዕከሉ ሥራ እንዳይቋረጥ አሜሪካን፣ጣሊያን፣ እንግሊዝ ላሉ ዶክተሮችን ስልክ ስጡኝና አናግራቸዋለሁ ሲሉም ነበር ይህን ሁሉ ግን አሳቸው አያውቁም። ከነቁና ከሕክምናው በኋላ ሲነገራቸው ብቻ ነው የተረዱት። ታዲያ እኚህ ሰው እግዚአብሔርን ለማመን ሎጂክ አያስፈልገኝም በጭፍኔ /Blindly / ነው። ማመን የምፈልግ ቢሉ ያስደንቃል /ፍልስምና 1/ ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ /ነሐሴ 2004/

አንተ(ቺ) የማላውቀውን ዝም ብዬ እንዴት ነው የምቀበለው ልትል(ዪ) ትችል(ዪ) ትችል(ዪ)ይሆናል በክርስትና ከማመን የሚቀድም እውነት የለም።

የሰው ልጅ ሕያዊት፣ ነባቢትና ለባዊት ነፍስ ስላለችው በዚህች ነፍሱ ምክንያት በተሰው የተፈጥሮ እወቁቱ በፍኖተ አዕምሮ በእግረ ልቡና(በአሳቡ) ተጉዞ አምላኩን ወደ ማወቅ ሊደርስ

ይችላል። ልክ እንደ አባታችን አብርሃም ማለት ነው። አብርሃም የመገዛትና የማምልክ ናፍቆትና ጥማቱን በቀላሉ ለማስረከብ አልወደደም ከሁሉ በላይ የሆነ ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ እንዳለ ከአመነ በኋላ "አምላከ ፀሐይ ተናበበኒ" ፤ የፀሐይ አምላክ ተናገረኝ፣ተገለጥኝ፣ቅረበኝ አምላክ ሁነኝ... › በማለት የጸለየው አብርሃም እንዲህ ለማለት የበቃው ሁሉቱ ነገሮች ተባብረውለት ነው እምነቱና ዕውቀቱ የጀመረው ግን ከማመን ነው።

ስለዚህ ሃይማኖት አውቀው የሚያምኑት ወይም የሚቀበሉት ሳይሆን አምነው የሚቀበሉት ወይም የሚያውቁት ነው። ሃይማኖታችንን በምርምር /ቤተሙከራ/ እያረጋገጥን የምንቀበለው ቢሆን ሃይማኖት ብለን ልንጠራው አንችልም። ምክንያቱም የቤተ ሙከራው ውጤት በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ሲሆን ሃይማኖት ግን ከዕውቀት በላይ ነው ሃይማኖት በዕውቁት ያውም በሰው ዕውቀት አይመረመርም። ለምን ብለህ(ሽ) መጠየቅ ትችላለህ(ያለሽ) ምክንያቱ ከዚኽ አለ።

ሀ. ዕውቀት ሁሉ ፍፁም አይደለም

የሰው ልጅ እውቀት መቼም ቢሆን ፍፁም አይደለም የመስኩ ተመራማሪዎች የአንድ ሰው ዕውቀት በጣም ውሱን እንደሆነ ሲያራሩ ሰው ሁልጊዜም በመማር ሒደት ውስጥ ነው ይላሉ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን የዕውቀት ውሱንነታችንን ሲገልጽ “ከዕውቀት ከፍለን /In part/ እናውቃለንና ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና”። ብሏል /1ኛ ቆሮ. 13 ፡9/ ሐዋርያው ይኼ ዕውቀታችን እንደ ዕድሜያችንና ዕድገታችን እየተሻሻለ እያደገ እንደሚሔድ ካስረዳን በኋላ ፍፁም የሚሆነው ያውም በራሱ መጠንና ልክ ብቻ /በነፍስ ዕውቀት አቅም/ ከሞትን በኋላ እንደሆነ ያስተምረናል። እንዲህ ሲል ".....ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቀለሁ በዚያን ጊዜ ግን /ከሞት በኋላ ባለ ሕይወት/ እኔ ደግሞ እንደታወቅሁ አውቃለሁ" ቁ. 12

ለ. ዕውቀት ሁሉ የሚሻር ስለሆነ

የዚህ ዓለም ዕውቀት /Theory/ ሁሉ መሠረቱ የሰዎች ስምምነትና ግብብነት ስለሆነ በአንድ ወቅት ሰዎች ተስማምተው ‹ ዕውነት› ያሉትን በሌላ ጊዜ ደግሞ ስምምነታቸውን በጥናትና ምርምርም ሲያፈርሱት ‹ ውሸት› ሊሉት ይችላሉ ሳይንሱም የሚለን ይህንኑ ነው። ምክንያቱም ሳይንስ ማለት እኮ ጥበብን፣ ዕውቀትን፣ ጥናትን፣ መሠረት አድርጐ አንድን ነገር አረጋግጦ መቀበል ነው። /Science is Systematic Study anything that can be examined,Tested,and Verified/ ስለዚህ ሳይንስ ሒደት ነው።

አንድን ነገር በአንድ ዓይነት ሁኔታ ፈርጆ ለዘንተ ዓለም(እስከመጨረሻው) ይህ ነው አይልም። ለዚህ ብዙ ማሳያዎችን ከሳይንሱ ግኝቶች መጥቀስ ይቻላል ለምሳሌ በልጅነታችን ዘጠኝ

ናቸው ተብለን የተማርናናቸው ፕላኔቶች /planets / ዛሬ ወደ አሥራ አንድ የመድረሳቸው ውጤት የኑሮ ውድነት አይደለም። የዚህ ዓለም የአንድ ዘመን ዕውቀት በሌላ ዘመን ዕውቀት የመሻሩ እውነት እንጂ። በጣም የሚገርም ሌላም ጉዳይ አለ ዓለም አንዳንዴ ዕውቀት ብሎ የሚነግረን በሳይንስ እንኳን ያልተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑ ነው።

እስኪ አንድ ምሳሌ እንደወረደ እናቅርብላችሁ ጉዳዩ በሐመረ ተዋሕዶ ዓመታዊና ልዩ መጽሔት የቀረበ ነው እንዲህ ይላል ፦

"በ1871 በታተመውና "The Descent of man"በተባለው መጽሐፉ ዳርዊን የሰው ልጆችና ጦጣዎች ከአንድ የጋራ ዝርያ የተገኙ ናቸው አለ።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የዳርዊን ደጋፊዎች ይህንን መላምት ወይም እምነት በመረጃ ለማስደገፍ ብዙ ሞክረዋል ይህ የዳርዊን መላምት ትክክለኛና ሳይንሳዊ ሀቅ የሚመስላቸው ብዙ ሰዎች አሉ በተለይም ደግሞ አውቀው ለመታለልና የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት ላለመቀበል ምክንያት የሚፈልጉ ሰዎች ይህን የዳርዊንን ግምት እንደ እውነታ አድርገው ሰንፍናቸውን ለማስደገፍ ይጠቀሙበታል ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ሳይቀሩ የክርስትናን አስተምህሮ ከዚህ የዳርዊን ግምት (ቲዎሪ)አንጻር ለመቃኘትና ለማስታረቅ የሚሞክሩ ብዙዎች ናቸው... ብዙውን ጊዜ ተራው ሰው የሰው ዘር ዝግመተ ለውጣዊ አመጣጥን በተመለከተ የሚወራው ወሬ በሳይንስ ማስረጃና በጭብጥ የተደገፈ እንደሆነ ያስባል እንጂ ስለዚህ ሁኔታ ብዙም አያውቅም።

ለዚህ የተሳሳተ ግንዛቤ ምክንያቱ በየመገናኛ ብዙኃኑና በተለያዩ መንገዶች ይህ ጉዳይ እንደተረጋገጠ እውነታ ተደርጎ ስለሚወራና ስለሚለጠፍ ነው ሆኖም በጉዳዩ ላይ እውነተኛ ባለሙያዎች የሆኑት ግን የሰው ዘር ዝግመተ ለውጥ ቲዎሪ ጉዳይ /The clim of human evolution/ ሳይንሳዊ መሠረት እንደሌለው ያውቃሉ።የሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ፖሌዎ አንትሮፖሎጂስት ዳቪድ ፒልቢም እንዲህ ይላል "ከሌላ የሙያ ዘረፍ የሆነ አንድን ጎበዝ ሳይንቲስት ብታመጣውና በዚህ ዙሪያ ያሉንን መናኛ ማስረጃዎች ብታሳየው በእርግጠኝነት አይ ይህንስ ተወው እዚህ ግባ የሚባልና ለመቀበል የሚያስችል በቂ ነገር አይደለም ይላል" /Richard E.Leaky,The Making of Mankind, Sphere Books Limited,Barcelona,1982,p.43/ እንዲሁም ዊሊያም ፊክስ የተባለው በፖሌዎ አንትሮሎጂ ላይ መጽሐፍ የጻፈው እንዲህ ብሏል "እስካሁን እንዳየነው ሰው እንዴት እንደመጣ ያለምንም ጥርጥር እናውቃለን ብለው ለመናገር ድፍረቱ ያላቸውና ይህንኑ በፕሮፖጋንዳ የሚያናፍሱ ብዙ ሳይንቲስቶች አሉ የሚያሳዝነው ግን መረጃ የሌላቸው መሆኑ ነው" (William R.Fix, The Bone peddlers, Macmillan publishing

Company, New York, 1984,p150-153)" (ሐመረ ተዋሕዶ (የሐመር መጽሔት ልዩ ዕትም)በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን፣ነሐሴ ፳፻፪ዓ.ም አዲስ አበባ)

በርካታ ሰዎች በሳይንስ እንኳን ያልተረጋገጡ እውነት የሚመስሉ ግን ከእውነት የራቁ ብዙ ጉዳዮችን ተቀብለው ሲያበቁ ከእውነት በላይ እውነት የሆነውን እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራዎች አንቀበልም ብለው በሚሻር ዕውቀታቸው ሲሞግቱ አይገርምህም(ሽም)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የዚህ ዓለም ዕውቀት የቱን ያህል የሚያስደንቅና እፁብ የሚያስብል ቢሆንም እንኳን ጊዜያዊና የሚሻር መሆኑን ሲነግረን እነዲህ ይለናል "ከዕውቀት ከፍለን እናውቃለንና ከትዕቢትም ከፍለን እነናገራለንና ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል።....."ኖቆሮ. 13፡9-10/

ስለዚህ በዚህ ፍፁም ባልሆነና ተለዋዋጭ በሆነ በየጊዜው በሚሻር ዕውት ከውቀት ሁሉ በላይ የሆነውን እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ነገር በመጠናችን የምንረዳበትን ሃይማኖት መመርመር እንችላለን ብለን ብናስብ የማይሆን ነገር ስለሆነ ያለን ብቸኛ አማራጭ ዝምብለን /በእምነት/ መቀበል ብቻ ነው። አንድ ሰው በዕውቀት ብቻ ሙሉ ሰው ሊሆን አይችልም በእምነትም ጭምር እንጂ (ኤፌ.4፡13) አንድ ሰው ሃይማኖቱን በእምነት ተቀብሎ የእግዚአብሔርንም መኖር በእምነት ተቀብሎ በዚህ ዙሪያ የተጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍትን እየመረመረ እምነቱን በዕውቀት ሊሸልምና ሊያስጌጥ ይችላል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ቅዱስ ልጁ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት እንዲህ ነበር ያለው "ከሕፃንነትህ ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል"። በማመን አውቀሃል መባሉን ልብ ይሏል /2ኛ.ጢሞ 3፡15/ መዳን ሁልጊዜም የሚገኘው በማመን ነው እንጂ በማወቅ አይደለም ምክንያቱም የሚያድነው እምነታችን እንጂ እውቀታችን ስላልሆነ። ጌታም በወንጌሉ ሰዎችን ከተለያዩ ክፉ ነገር ሲታደጋቸው እምነትህ /ሽ/ አድኖሀል/ሻል/ ይል ነበር።

4ኛ. <u>በሥራ የሚተረጉሙት ነው፡-</u>

ይህ ሥራ መልካም ሥራ ሲሆን መልካም የሚያሰኘውም በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ሰብዕ /ሰው/ ማለትም እግዚአብሔርንና ሰውን በመውደድ ላይ ተመስርቶ የሚሠራ ስለሆነ ነው። ከላይ የሃይማኖትንና እምነትን ልዩነትና አንድነት ስናብራራ ሃይማኖትን እምነት ብለን ለመግለጽ ከሚያስገድዱን አንዱና ዋነኛው ጉዳይ ተግባር ነው።

ሃይማኖት ጥላ ሥር ያለ ሰው እምነት አለው የለውም ተብሎ የሚመዘነው ሃይማኖቱ የሚፈቅደውን ሥራ ሠርቶ በመገኘቱና ባለመገኘቱ ነው። እንጂ የሃይማኖቱ ልኬት ከደሙና ካጥንቱ ናሙና ተወስዶ በላብራቶሪ /ቤተ ሙከራ/ ሊሠራና ሊረጋገጥ አይችልም። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ እንዳስረዳው ሃይማኖትን ከሥራ ለይቶ ማሳየት አይቻልም ሃይማኖትን በሥራ ማሳየት ግን ይቻላል። /ያዕ 2፡18/ ስለዚህ በሃይማኖት የሚተገበር መልካም ሥራ ሁሉ ማመንን ብቻ ሳይሆን መታመንን ይገልጣል ማለት ነው።

በጥቅሉ ሥራ የሌለው በሥራ የማይገለጥ ሃይማኖት የለም አይኖርምም 1ኛጢሞ.1፡18፣ ራዕ.22፡12፣ማቴ 25፡30-46፣ዮሐ. 5፡29 "ያለ ሃይማኖት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም" የተባለው እኮ ሃይማኖት ስላለን ብቻ ሳይሆን ይህን ሃይማኖታችንን በምግባር ስንገልጠው ነው። /ዕብ11፥6/ በነገራችን ላይ አንድ ሰው ወዳንተ(ቺ) መጥቶ ሃይማኖትህን(ሽ) አሳየኝ(ዪኝ) ቢልህ ልታሳየው(ዩው) ትችላለህ(ያለሽ)? ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ግን ያለምግባር ሃይማኖትን ማሳየት እንደማይቻል ይነግርሃል(ሻል)።"ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።"/የያዕ.መልዕክት2÷26/

5ኛ.<u>የማይታየውን የሚያሳየን ረቂቅ መሣሪያ ነው</u>

በዚህ ዓለም በሞላው ሥጋዊ ዕውቀት አይታዩም፣ አይያዙም፣ አይጨበጡም የምንላቸው በርካታ ነገሮችና አይታመኑም፣ አይከሰቱም፣ አልተከሰቱም የምንላቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ። ይህን ሁሉ ለማለት ያሰገደደን ከላይ እንዳብራራነው ከእኛ ከሰዎች ልጆች የዕውቀት ውሱንነት የተነሳ ነው ለምሳሌ ነፋስ፣ነፍስ፣መላእክትን ብንወስድ ከነፋስ ነፍስ ትረቃለች፣ ከነፍስ ደግሞ መላእክት ይረቃሉ ይሁን እንጂ ርቀታቸውና (መርቀቅ) አለመዳሰሳቸው ለእኛ ለፍጡራኑ እንጂ ለፈጠራቸው አይደለም። የፈጠራቸውና ያስገኛቸው እሱ ስለሆነ ያያቸዋል፣ይዳስሳቸዋል፣ይገዛቸዋል። ይህንን ባሕርይውን ሲገልጠው ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ብሏል "ውኃዎችን በእፍኙ የሠፈረ ሰማይንም በስንዝር የለካ የምድርንም አፈር በመስፈሪያ ሰብስቦ የያዘ ተራሮችን በሚዛኖች የመዘነ ማን ነው)"ሲል ይጠይቃል ከእግዚአብሔር ከፈጠራቸው በስተቀር በእውነት ይህን የሚያውቅና የሚያደርግ ማን ነው) /ኢሳ.40፡12/ ሙሴ በወቅቱ በሥጋዊ ጥበብና አእምሮ እንኳንስ ሊታይ ሊታሰብ የማይቻለውን የኋላውን ክብሩን ቀድሞ የተመለከተው በሃይማኖት ነው።

"... ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርኦን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ ከግብጽ ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበል መረጠ፤ ብድራቱን

/ክፍያውን ውጤቱን፣ የኋላውን ክብር/ትኩር ብሎ ተመልክቷልና"/ዕብ.11፡24-26/ ለዚህ ነው ፍፁም ሃይማኖት የሌለው ሰው ክርስትናን ጀምሮ የሚያቋርጠው፣ በክርስትና ጉዞ ቶሎ የሚዝለው።

እንግዲህ በሃይማኖታችን ረቂቁን ፣ አግዝፈን፣ የራቀውን አቅርበን የነገውን እንደ ዛሬ የምናይ ከሆነ ሃይማኖታችንንን በመልካም ሥራ ማሳደግና ማበልጸግ እንደሚጠበቅብን ላፍታም መዘንጋት የለብንም / 2ኛ ጴጥ.1፡5-9/ ተጨማሪ ትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ /ብርሃኑ አድማስ /ዲ/ን/ 2002 ዓ.ምከገጽ2-9 ያለውን ይመልከቱ።

1፡4. ሀልዎተ እግዚአብሔር

ከዚህ በፊት ይህንን ቃል ሰምተኸው(ሸው) ታውቃለህ(ቂያለሽ) እግዚአብሔር በእርግጥ አለን? ለመኖሩ ማረጋገጫኽ(ሽ) ምንድን ነው? ለራስህ(ሽ) መልስ(ሺ)

ሀለወ ለሚለው ቃል መሠረቱ ግዕዝ ሲሆን ትርጉሙም አለ፣ ኖረ ፣ነበረ ማለት ነው በዚህ መሠረት ሀልዎተ እግዚአብሔር ስንል የእግዚአብሔር መኖር፣ ኑባሬ፣ አኗኗር ማለታችን ነው።

ለሃይማኖት መኖር መሠረቱ የእግዚአብሔር መኖር ነው፤ እግዚአብሔር የሌለው ሃይማኖት ሊኖር አይችልም። ሃይማኖት ካለ እግዚአብሔር አለ ማለት ነው። ብዙዎች "እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት ቀርቦም ሳለ ጥሩት"። እየተባለ በስፍናቸው፣ ባለመመርመርና ባለማወቅ ችግራቸው ብቻ እግዚአብሔርን የለም ማለት ይቃጣቸዋል "ሰነፍ በልቡ አምላክ የለም ይላል።" እንደተባለ / መዝ53፥1ኢሳ.55፡6/

እኛ ክርስትያኖች ብዙዎቹ ዓለማውያን ጠበብት አንድ ኃይል አለ። ብለው ሳያምኑበት /የሚጠሩትን/ ለራሱ አስገኝ የሌለውና ዘመን፣ ዓመት፣ ዕለት፣ ወር የማይቆጠርለትን፤ ከጥንት፣ ከዘመን፣ ከዓመት፣ ከወርና ከዕለት አስቀድሞ የነበረውን፤ ፍጥረቱን ሁሉ ፈጥሮ የሚያስተዳድረውንና ኋላም በሥርዓት የሚያሳልፈውን ዘለዓለማዊ አምላክ እግዚአብሔርን፤ ነበረ፣ ይኖራል፣ አለ፣ ብለን እናምናለን። እግዚአብሔርም ይህንንን ሀለዎቱን በተለያየ መልኩ ገልጾልናል። ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

እግዚአብሔር ራሱን ለዓለም ያስተዋወቀበት መንገድ

እግዚአብሔር አምላክ ለዓለም ራሱን ያስተዋወቀው ወይም የገለጠው በሦስት ዋና ዋና መንገዶች ነው፡፡ እነሱም፦፡፡

1. በሥነ ፍጥረት /ፍጥረተ ዓለም/
2. ቃል በቃል ከሰው ጋር በመነጋገር
3. በመንፈስ ቅዱስ መስተናግርነት(አናጋሪነት) በተጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍት፡፡ እነዚህ ሦስት ነጥቦች ዘርዘር ብለው ስለተቀመጡ እስኪ በጥሞና ተመልከታቸው(ቺያቸው)

በሥነ ፍጥረት

እግዚአብሔር በሚታውና በማይታየው፣ በሚዳሰስና በማይዳሰሰው ሥራው የዚህ ሁሉ ዓለም አስገኚና መጋቢ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይኽ ማለት የፈጠረው ፍጥረት /ሥራው/ ሀልዎቱን /መኖሩን/ ይመሰክርለታል፡፡ ልክ በአንድ ሕንፃ ሐናፂው(የሕንፃው ሠሪ) እንደሚታወቀው ሁሉ ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር አምላክ በዚህ ዓለም የምናያቸውን ሰማይን /ጠፈርን/ እና ምድርን፣ እንሰሳትንና አራዊትን፣ አዝርዕትንና አትክልትን፣ በአጠቃላይ የሰውን ልጅ ጨምሮ በውኃ /በባሕር/ እና በየብስ ያሉ በክንፍ የሚበሩ፣ በእግር የሚሸከረከሩና በደረት የሚሳቡ ፍጥረታትን፤ እንዲሁም ፀሐይ፣ ጨረቃና፣ ከዋክብትን ሁሉ የፈጠረ ነው፡፡ ይህ ብቻም አይደለም የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ በከሀሊነቱ የሚመግብና የሚያስተዳድር ብቸኛ አምላክ ነው፡፡ እስኪ ይህንን የመጽሐፍ ክፍል በእርጋታ አንብበው(ቢው)

ለአንተም(ቺም) ሆነ ለመላው የሰው ልጆች በእነዚህ ፍጥረታት ብቻ የእግዚአብሔርን ፈጣሪነትና መጋቢነት በሚገባ መረዳት ቀላል ነው፡፡ ምክንያቱም “የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘለዓለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህ እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የሚያስተውለውም ልባቸው ጨለመ ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮዎች ሆኑ”፡፡ ሮሜ. 1፡20 ተብሎ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ስለሚመሰክር፡፡

እነዚህ ፍጥረታት ተፈጥረው መታየታቸውና የተፈጠሩበትን ህግና ሥርዓት ሳይለቁ በአግባቡ መኖራቸው የፈጠራቸው መኖሩንና፣ ፈጥሮ እንዳልተዋቸው፣ እንደሚመራቸውና እንደሚቆጣጠራቸው የሚመሰክሩ ህያው ሃውልቶች ናቸው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱን ያለ ምስክር እንዳልተው የሚገልጽልን ይህንኑ ሲያስረዳን ነው። ግ.ሐ.ዋ 14፡17 ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ለዚህች ዓለም አስገኝና መጋቢ የላትም የሚሉ መነናውያንን /manisen/ በገሰጸበት የመዝሙር ክፍል ተዘርግተው በመታየታቸው ሰማይና ምድር የእግዚአብሔርን ጌትነቱን ፈጣሪነቱን የሚመሰክሩ በመሆናቸው "ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር፤ ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፣ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል"። ሲል ተናግሯል /መዝ 18፡1/ ይህንን እንድትረዳው(ጂው) አንድ ተፈጸመ ታሪክ እናንሳ።

አንድ ተማርኩ አወቅሁ ተራቀቅሁ ባይ ዘመነኛ የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት በፍጥረቱ የሚረዳ አንድን የአገራችንን የዋህ ገበሬ እነዚህን እግዚአብሔርን የምታመልክባቸውን መጽሐፍቶችህን ሁሉ ቀድጀ ብጨርስብህ እግዚአብሔርን በምን ታመልክዋለህ) ሲል አንደበቱን ያላቅቅበታል።

የዋሁና በሃይማኖቱ ጠንካራ የሆነው ገበሬ የዋዛ አልነበረምና "አይ ጌታው ሰማይን ከነግሱ(ጓዙ) ምድርን ከነልብሱ ቀደህ ትጥልብኝ ይሆን)" በማለት የፍጥረታቱን የተገለጠ መጽሐፍትነት መስክሯል።

ከመጻሕፍተ መነኮሳት አንዱ የሆነው ማር ይስሐቅም ይህንኑ አሳብ እንዲህ ሲል ያጠናክረዋል። "የእግዚአብሔርን ህልውና ልታወቅ ከወደድህ መምህርና ምስክር ሆኖ እግዚአብሔርን ወደማወቅ የሚመራህ ሥነ ፍጥረት አለልህ።" /ማር ይስሐቅ ምዕ.1 አንቀጽ 2/ መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይላል "ዓለሙም በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠረ ባለመኖር ምንም አይታይ የነበረም ወደ መኖር መጥቶ እንደታየ እናውቃለን።" ዕብ 11፡3፣ግ.ሐ.ዋ 17፡26

ቃል በቃል ከሰው ጋር በመነጋገር

እግዚአብሔር አምላክ በአርአያውና በአምሳሉ ከፈጠረው የሰው ልጅ ጋር ቃል በቃል በመነጋገር ራሱን ገልጧል። ወይም ህልውቱን(መኖሩን) አስመስክሯል። ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ እንደምናገኘው ገና ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት ከተነሱ ነቢያትና ታላላቅ አባቶች ጋር ያደረጋቸው የቃል በቃል ንግግሮች ለዚህ ዋና ማስረጃዎች ናቸው ጥቂቶቹን ተመልከት(ቺ)

- "እግዚአብሔር አምላክ ሰውን እንዲህ ሲል አዘዘው ከገነት ፍሬ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምና ክፋን ከምታሳውቀው ዛፍ አትብላ ከእርስዋ በበላህ ቀን ሞተን ትሞታለህና"። (ዘፍ.2፡16)

- “እግዚአብሔር ኖኅን ልጆቹን ባረካቸው እንዲህም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት” ።(ዘፍ 9፡1)
- “እግዚአብሔርም ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር”።ዘጸ. 33፡11 ሌላስ እንተ(ቺ) የምታስታውሰው(ሺው) ተመሳሳይ ንግግር ይኖር ይሆን ልታክልበት(ይበት) ትችላለህ(ያለሽ)።

እግዚአብሔር አምላክ ከሰው ልጆች ጋር ቃል በቃል ይነጋገር የነበረው በገሃድ(በግልጥ) ሆኖ በራዕይና በህልም ነው። የህልምና የራዕይ ልዩነት ይገባሃል(ሻል) ግን? በቀላሉ ሲቀመጥ ህልም ተኝተህ(ሽ) የምታየው(ዩው) ሲሆን ራዕይ ደግሞ ያለእንቅልፍ በገሃድ የምታየው(ዩው) ነው።

ይህም በመሆኑ ለሰው ልጅ እግዚአብሔርን ማወቅ ከባድ አልሆነበትም ነበር። ምክንያቱም የሚያናግራቸው ቃል በቃል ከመሆኑም በላይ ማንነቱንና ባሕርይውንም ይገልጽላቸው ስለነበር ነው።"እግዚአብሔርም ሙሴን ያለና የሚኖር ወደ እናንተ ላከኝ ትላለህ" አለው። ተብሎ እንደተጻፈ ማለት ነው።

በመንፈስ ቅዱስ መስተናግርነት (አናጋሪነት)ና አነሳሽነት በተጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍት

መጽሐፍ ቅዱስን ገልጠን ከቀዳሚ ገጹ ተነስተን ማንበብ ብንጀምር “በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ /Created/” ብሎ በንባቡ ብቻ ስናየው በትንሹ ሦስት ነገር ይነግረናል፡-

1ኛ. ሰማይና ምድር መኖራቸውን

2ኛ. ሰማይና ምድር የተፈጠሩ የተገኙ መሆናቸውን

3ኛ. የሰማይና ምድር አስገኝና ፈጣሪ እግዚአብሔር መሆኑን።

ስለዚህ ይህ ዓለም ድንገት እንደ ብልጭታና እንደ እንቡጥ አበባ ፈንድቶ የተገኘ ሳይሆን በእግዚአብሔር የተፈጠረ መሆኑን እናምናለን ማለት ነው። ነቢዩ ኤርሚያስም በትንቢቱ እንዲህ ሲል ፈጣሪነቱን ያሰረዳል “ምድርን በኃይሉ የፈጠረ ዓለሙን በጥበቡ የመሠረተ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው”(ኤር. 51፡15፣ ራዕ.10፡6 መዝ.23፥1-3፣መዝ.101፥25፣ መዝ. 145፥6)

የእግዚአብሔርን ሀልዎት የሚያስረዱ ብለን ያነሳናቸው ሦስት ነጥቦች የሚመሩን ወደ አንድ ነጥብ ነው። ወደ ሥነ ፍጥረት። ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱን የገለጠው ከሰው ልጅ

ጋር ባደረገው የቃል በቃል ንግግር ነው ስንል ሰው ከሥነ ፍጥረቱ አንዱ ነው። በሥነ ፍጥረቱ ይታወቃል ስንልም ያው ስለ ሥነ ፍጥረት እያወራን ነው።

በመንፈስ ቅዱስ መስተናግርነት የተጻፉትም ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያሰረዱን ፈጣሪነቱን ነው። ስለዚህ ፍጥረታቱ በሦስቱም ነጥቦች እግዚአብሔርን ለመግለጥ ማዕከል ናቸው ማለ ነው።

1.5. በክርስትና አስተምህሮ እግዚአብሔር ማነው?

እውነት እግዚአብሔር ማነው? እነዲህ ብለህ(ሽ) ራስህን(ሽን) ጠይቀህ(ሽ) ታውቅ(ቂ) ይሆን? ይህንን ርዕስ ማንበብ እንዲህ ብትጀምረውስ(ሪውስ)? የአንድ መምህር አሳብ ነው እስኪ ልብ ብለህ አንብበው(ቢው)።

መምህሩ በኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ መምህር የሆኑት መጋቤ ሐዲስ እሸቱ ዓለማየሁ ናቸው። እንዲህ ይላሉ

“መጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ቁጥር አንድ ሲጀምር ስለ እግዚአብሔር አይደለም የሚነግረን በሥራው ነው የሚጀምረው ራሱ እግዚአብሔር ማነው? የተብራራ ነገር የለም በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ይላል መጽሐፍ ስለ እግዚአብሔር የሚሰጠን ማብራሪያ የለም እግዚአብሔር ከህሊና ከዕውቀት ከጊዜና ከቦታም በላይ ነው”።/ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ ፍልስምና 2ሐምሌ 2004 ዓ.ም ገጽ20/ከዚህ አሳብ ምን ተረዳህ(ሽ)

እግዚአብሔር ማነው የሚለውን ጥያቄ የምንመልሰው በእኛ አዕምሮ መጠንና ልክ መጽሐፍ ቅዱስ በገለጸው መንገድ ብቻ መሆኑን የተረዳህ(ሽ) ይመስለናል።

ከላይ ለማስቀመጥ እንደሞከርነው እግዚአብሔር ራሱን በልዩ ልዩ መንገድ ገልጾልናልና ማንነቱን በገለጸልን መንገድና መጠን ብቻ መናገር እንችላለን። በዚህ መሠረት እግዚአብሔር የሚለው ስም አምላካችን በባሕርይ ግብሩ የሚጠራበት የግብር ስም ሲሆን ማንነቱም በክርስትና አስተምህሮ እንደሚከተለው ይብረራል።

በነገራችን ላይ አንተ(ቺ) በግልህ(ሽ) እግዚአብሔር ብለህ(ሽ) የምታምነው(ኚው)፣ ወይም ደግሞ ሌሎች ሰዎች እግዚአብሔር ብለው የሚያምኑት የሰማኽ(ሽው) ነገር ካለ ያንን "አግዚአብሐር " ተብዬ በነዚህ ከታች በተዘረዘሩት መለኪያዎች ማለትም የእግዚአብሔርነት መገለጫዎች አስገብቶ ማየትና መለካት ይቻላል። በትምህርተ ሃይማኖት የእግዚአብሔርነት መገለጫዎቹ እነዚህ ስለሆኑ።

ሀ./ እርሱ ሌላውን የሚመረምር በሌላው ፍጡር የማይመረመር የማይወሰን ረቂቅ መንፈስ ዘሥሉጥ ላእለ ኩሉ /በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው /የሁሉ ንጉሥ፣ መሪና አስተዳዳሪ ነው። "እግዚአብሔር ታላቅ ነው እኛም አናውቀውም የዘመኑም ቁጥር አይመረመርም" እንዲል ኢዮ36፡ 36

በተጨማሪም እነዚህን መጽሐፍቶች ይመልከቱ /ፍኖተ እግዚአብሔር ብፁዕ አቡነ ቶማስ ሊቀ ጳጳሳት 1990 ዓ.ም ፤/መሰረተ ሃይማኖት ሊቀ ትጉሃን ኃ/ጊዮርጊስ ዳኘ 2004 ዓ.ም/እና /ትምህርት ሃይማኖት መግቢያ ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ ጥቅምት 2002 ዓ.ም/

ለ/.እርሱ ሁሉን ቢያመጣ፣ ቢያስገኝ፣ ቢያሳልፍ እንጂ ለእርሱ አምጪና አስገኝ የሌለው። ህልው ዘልዓለም። /ለዘልዓለም የሚኖር/ "አራቱም እንስሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሏቸው በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዓይኖች ሞልተውባቸዋል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና ያለው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፍም" እንዲል /ራዕ4-811-17-19/

ሐ/.እርሱ አልፋ ወዖ ያለና የሚኖር / the beginning and the end/የሆነ፣ በባህርይው አንድነትና ሦስትነት ያለው፣ ቀዳማዊ ወደኃራዊ "ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ" እንዲል ራዕ 22-14 ኢሳ43-10 ሐዋ14-8-19

መ/.እርሱ ገባሬ ኩሉ ወከሀሌ ኩሉ የሚታየውንና የማይታየውን በገዛ ስልጣኑ በከኃሊነቱ ያለ አማካሪና ያለ እቅድና (ያለፕላን)አምሳል መርገፍ ያስገኘ "የእግዚአብሔርን መንፈስ የያዘ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማነው ነው? ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ? ወይስ ማን መከረው? እንዲል" /ኢሳ 40፥13/ ይህ ብቻ ሳይሆን የፈጠረውን ፍጥረት ኋላም ሊያሳልፈውየሚችል ሁሉ የእርሱ የሆነ ምንም ያልጎደለው ባለፀጋ እጅግ ጠቢብና ብቸኛ አንድ ኃይል ወይም ጌታ ነው።

"ውኖችን በእፍኙ የሰፈረ፣ ሰማይንም በስንዝር የለካ፣ የምድርንም አፈር በመስፈሪያ ሰብስቦ የያዘ ፣ተራሮችን በሚዛን ኮረብቶንችንም በሚዛኖች የመዘነ ማን ነው" እንዲል ኢሳ40-12 በክርስትና የሚሰበከው፣የሚታመነው፣ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን በቃላቸውም ሆነ በጻፏቸው ቅዱሳት መጽመጽ የመሰከሩለትና በዙዎቹ በሰማዕትነት ያለፉለት እግዚአብሔር መበጠኑ ሲገለጥ ይህን ይመስላል። ይህ አግዚአብሔር ልዩ ልዩ የባሕርይ መገለጫዎችም አሉት። ወደቀጣዩ ንባብ ከማለፍህ በፊት እስኪ የምታውቀውን ያህል የእግዚአብሔርን ባሕርይ አስቀምጥ(ጨ)

1.6. የእግዚአብሔር ባሕርያት

ከላይ በዝርዝር እንዳየነው እግዚአብሔር በባሕርይው የማይመረመር ቢሆንም ባሕርይው የሚገለጥባቸው መገለጫዎች ብዙ ናቸው። ይሁን እንጂ እኛ ስለባሕርይው የምንናገረው በመጠናቸን ከተገለጠለን ውስጥ ጥቂቱን ነው። ይህም የሚሆነው የእኛ ሕሊና መሸከም የማይችለው ባሕርይ ስላለው ብቻ ሳይሆን ሰው መረዳት የቻለውን ያህል እንኳ የሚገልጽበት ቋንቋ ስለሌለው ጭምር ነው። ቅዱስ ዮሐንስ "ወዳጆች ሆይ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን"(1ኛ ዮሐ 3፥2)። በማለት እንኳንስ የእግዚአብሔር ባሕርይ ለሰው የተዘጋጀውን ክብርንም ቢሆን ከዕለተ ምጽአት(ክርሰቶስ ዳግመኛ ለፍርድ የሚመጣበት ቀን) በፊት ከገናንነቱ የተነሣ ማወቅ እንደማይቻል ገልፆልናል። (ዲ/ን ብርሃኑ አድማስየትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ ጥቅምት 2002ዓ.ም)

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በራሱ ፈቃድና በራሱ መንገድ በንጽሕናና በቅድስና መስመር ለሚጓዙ ልጆቹ ሁሉ ረቂቅ ምስጢራትንና ራሱንም ጭምር ይገለጣል። "ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና" እንዲል። (ማቴ 5፥8)

የእግዚአብሔር ባሕርይ ስንል የራሱ ብቻ የሆነ ገንዘቡ፣ ከማንም ያልወሰደው፣ለሌላው ፍጡር ቢሰጠው የማይነድልና የማይመረመር ማለት ነው። የፈጣሪ ፍጡራን መጋቢ ዓለማት የልዑል እግዚአብሔር ባሕርይ አንዲት ናት ብርዝ፣ ድልዝ፣ ክልስ፣ ስርዝ፣ ቅልቅል፣ ቅይጥ ፣ የሌለባት ብዙ ሰዎች ስለ ልዑለ ባሕርይ ስለ እግዚአብሔር ሕልውና ለማጥናት ሲሞክሩ እግዚአብሔር ከሥነ ፍጥረት በፊትም ሆነ ከሥነ ፍጥረት በኋላ እንዴትና ወዴት እንዳለና እንደነበረ ለማወቅ ብዙ ይቸገራሉ።

ነገር ግን የፍትረቱ ሁሉ አስገኚና የነገሮች ሁሉ ጀማሪ የሆነው ኃያሉ አምላክ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በቦታ ተወስኖ እንዴትና ወዴት እንዳለና እንደ ነበር ተገልጾ ከሥነ ፍጥረት በፊትም ሆነ አሁን በቅዱሳት መጻሕፍት አልተጻፈም። አልተነገረምም። (አቡነ ቶማስ ሊቀ ጳጳስ ፍኖተ እግዚአብሔር 1990 ዓ.ም)

እግዚአብሔር በባሕርይው አንድነትና ሶስትነት ያለው አምላክ ሆኖ የማይለውጥ፣ የማይወሰን፣ ምሉዕ በኩለሄ (በሁሉ ቦታ ያለ)፣ ጻድቅ (እውነተኛ)፣ ዘለዓለማዊ፣ ከኃሌኩሉ (የሚሳነው የሌለ) ፣ወዘተ... ነው። ይህንንም ሁሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል በመንፈሳዊ ትውፊት ውስጥ በተለይም ኢትዮጲያውያን የእግዚአብሔርን ባሕርያት የሚገልጡባቸው በርካታ አባባሎችም አሏቸው።

ለምሳሌ

- "እሱ የከፈተውን ጉሮሮ እሱ ሳይዘጋው አያድርም" በዚህ ምሳሌያዊ ንግግር ውስጥ የእግዚአብሔርን መግቦት እንመለከታልን። በትክክልም እግዚአብሔር የፍጥረታቱ ሁሉ መጋቢያቸው ነው። "ቁራዎችን ተመልከቱ አይዘሩም አያጭዱም ዕቃ ቤትም ወይም ጎተራም የላቸውም እግዚአብሔርም ይመግባቸዋል። እናንተስ ከወፎች እንደ*ት* ትበልጣላችሁ" /ሉቃ.12÷24/

- በቀድሞ ጊዜ አንድ በደል የተፈፀመበት ሰው በአካባቢው ከተሰየመው ባሕላዊ ችሎት ደርሶ ከዳኛው ዘንድ አቤቱታውን ሲያቀርብ እንዲህ ብሎ ይጀምር ነበር። "እግዚአብሔር ያሳይዎ ክርስቶስ ያመልክትዎ" ይኼ ኃይለ ቃል በቀጥታ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ን ማዕመረ ኩሉ/ሁሉን መርማሪና አዋቂ/መሆን ነው። እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ስለሆነ ዳኞችን ይረዳቸዋል። እኔ እግዚአብሔር ለስው ሁሉ እንደ መንገዱ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ ኩላሊትንም እፈትናለሁ። /ኤር17፥10/

ተጨማሪ፦

እነዚህ ከታች ያስቀመጥናቸው የኢትዮጲያውያኑ አነጋገሮች ከእግዚአብሔር ባሕርያት የትኞቹን ይገልጣሉ? ብለህ(ሽ) ታስባለህ(ቢያለሽ) እስኪ በጥንቃቄ መርምራቸው(ሪያቸው)። በተጨማሪም ከሚመስሉህ(ሽ) ጓደኞችህ(ሽ)ና ከምታገኛቸው(ኚያቸው) የሃይማኖት መምህራኖችህ(ሽ) እየተወያየህ(የሽ)ና እየጠየክ(ሽ) ሌሎችንም አክልበት(ዪበት)

- "የሥራህን ይሥጥህ"
- "እግዚአብሔር ይማርህ"
- "ተሸፋፍነው ቢተኙ ገልጦ የሚያይ አምላክ አለ"
- "እግዚአብሔር ይመስገን"

ይህ የእግዚአብሔር ባህርይ ብለን የዘረዘርነውና ባጠቃላይ የእግዚአብሔርን ባሕርይ የምንገልጥባቸው ሌሎች ማሳያዎች ሁሉ በዚሁ መጽሐፍ ስላለውና ወደፊት ስለምትደርስበት(ሺበት) ምስጢረ ሥላሴ ትምህርት የሥላሴን አንድነት የሚያረጋግጥልህ(ሽ) ክፍል ነው። እዛ ላይ ስትደርስ(ሺ) አገናዝብና(ቢና) ተመልከተው(ቺው)። የሥላሴ ባሕርይ አንዲት ናትና።

1.7. ሥነ ፍጥረት ማለት

ሥነ ፍጥረት የሚለው ቃል የሁለት ቃላት ውሑድ ነው። ሥነ እና ፍጥረት ሥነ ማለት መነሻ ቃሉ ግዕዝ ሲሆን ሠናይ ብሎ ሠነየ ይልና መልካም ሆነ ተብሎ ይፈታል በመሆኑም ሥነ ፍጥረት ማለት መልካም፣ ውብ፣ ያማረ፣ የተስማማ፣ የበጀ ፍጥረት ማለት ሲሆን በሌላ መልኩ የፍጥረት መበጀት፣ የፍጥረት መስማማት / አንድ መሆን /፣ የፍጥረት መዋብ ማለት ነው።

1.8. ፍጥረት የምንላቸው እነማን ናቸው

ይህንን ከማብራራታችን በፊት ለአንባቢያችን ጥያቄ ማስቀመጥ ወደድን አንተ(ቺ) ፍጥረት የምትላቸው(ያቸው) ነገሮች አሉ ካሉ አፈጣጠራቸው እንዴት ነው? በተለያዩ አጋጣሚዎች ፈጠራና የፈጠራ ውጤቶች ሲባሉ ሰምተህ(ሽ) ታውቅ ይሆናል። ሰዎች ይኽንን ቃል የሚጠቀሙበት አግባብ ልክ ነው ብለህ(ሽ) ታስባለህ(ቢያለሽ) እስኪ በማሰላሰልና ስለፍጥረትና አፈጣጠራቸው የምታውቀውን(ቂውን) ሁሉ በማሰላሰል ጥቂት ቆይታ አድርግ(ጊ)

በክርስትና አስተምህሮ እኛ ፍጥረት ስንል በራሳቸው ያልተገኙ፣ በፈጣሪያቸው በእግዚአብሔር የተገኙ፣ በላይ በሰማይ በታች በምድር ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ረቂቅና ግዙፋን፣ የምናውቀቸውም የማናውቅቸውም፣የምናያቸውና የማናያቸው ማለትም በጥቅሉ መላው ዓለም / universe / ማለታችን ነው። በዚህ ዓለም ስንኖር እኛ የማናውቃቸውና የማናያቸው ፍጥረታት አሉ ቢሆንም ግን ከፈጠራቸው ከእግዚአብሔር የሚሰወሩና የሚረቁ ፍጥረታት በፍፁም የሉም "እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም" እንዲል/ዕብ 4፡13/

1.9. እግዚአብሔር ፍጥረታትን እንዴት ፈጠረ

ግሩም ጥያቄ ነው። እንዴት ይመስልሃል(ሻል)? በአንድ ጊዜ፣በተለያየ ጊዜ፣ ወይስ ሌላ የምትለው(ዩው) ነገር ይኖርሃል(ሻል)? ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር አምላካችን ፍጥረታትን በሁለት ዋና ዋና መንገዶች ፈጥሯል የመጀመሪያው እም ሀበ አልቦ ሀበቦ / ካልመኖር ወደ መኖር/ ማለትም ከምንም /ከባዶ/ ወደ ያለ ነገር ወይም ከባዶ በቀጥታ ፍጥረትን ፈጥሮ ማሳየት ይህንንም ከኢምንት ወደ ምንት ማምጣት ይሉታል ሊቃውንቱ በቀላሉ ለማስቀመጥ አስቀድሞ ካልተገኘ ነገር የተገኘ ማለት ነው። በዚህ ዓለም ያሉ ጠቢባን ነገሮችን ቀምረውና አዋሕደው

የሚያሳዩን ከተፈጠረው ነገር ተነስተው ነው። ጠቢበ ጠቢባን የሆነው አምላካችን እግዚአብሔር ግን ፍጥረታትን ከሌሉበት ወደ ሚኖሩበት በማምጣት ነው /እምህበ አልቦ ህበቦ/ ያልነው ይኽንን ነው።

ሁለተኛው መንገድ ግብር እምግብር የሚባለው ነው። ይኽም ማለት ከተፈጠሩት ፍጥረታት መልሶ ሌላ ፍጡር ማስገኘት ማለት ነው። ይህንን በምሳሌ ማሳየት ይቻላል ለምሳሌ ከምንም ነገር ያለ ነገር አድርጐ መፍጠር ስንል እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ የሚለው ንባብ የሰማይንና የምድርን መፈጠር ሂደት / process / አይነግረንም ስለዚህ ሰማይንና ምድርን ከዚህና ከዚህ ቀምሞና በዚህና በዚህ አድርጎ ፈጠራቸው ብሎ መናገር አይቻልም። ሰማይና ምድር የሉም ነበር ተፈጥረው ታዩ፣ተገለጡ። ይኼ እም ህቦ አልቦ ህበቦ ይባላል። ለሁለተኛው ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የሰው ልጅ ተፈጥሮ ነው እግዚአብሔር አምላክ የሰውን ልጅ የፈጠረው በዕለተ አሁድ ከተፈጠረ አፈር ነው " እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው.." (ዘፍ. 2፡7) ስለዚህ ምድር /አፈር/ አስቀድሞ የተፈጠረ በመሆኑ የአዳም አፈጣጠር ግብር እምግብር ነው ማለት ነው። ከተፈጠረ ነገር የተፈጠረ እንደማለት።

1.10. ፍጥረታት ለምን ተፈጠሩ

እግዚአብሔር እኛን የሰዎች ልጆችን ጨምሮ ፍጥረታትን ሁሉ ለምን እንደፈጠረ በሚገባ ተረድተኽ(ሽ) ይሆን? አንዳንዶች ያለፍጥረቱ መኖር ስለማይችል ነው ሲሉ ይደመጣሉ ይኼ ፍጹም ስህተትና ከላይ ያስቀመጥነውን የእግዚአብሔርን ባሕርያት ካለማወቅ የተነሳ የሚንጸባረቅ አሳብ ነው። ግን ለምን ተፈጠርኩ ብለህ(ሽ) ጠይቀህ(ሽ) ታውቅ(ቂ) ይሆናል? ጥያቄው ጥሩ ነው ምላሹን አሁን ልታገኘው(ኚው) ነው

በቅድሚያ መታወቅና መታሰብ ያለበት ጉዳይ አለ እግዚአብሔር ፍጥረታት ሳይፈጠሩ መኖር ይችላል። ፍጥረታትን መፍጠሩ የጎደለውን ሊሞላ፣ያለ ፍጥረት መኖር ስለማይችል፣ በጥቅሉ ለራሱ ብሎ አይደለም፤ እርሱ ፍጥረታትን የፈጠረበት ዓላማ በእርሱ ዘንድ የታወቀ የተሰወረና የተጠበቀ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶችን ማስቀመጥ ይቻላል።

1ኛ.ስሙን ለመቀደስና ክብሩን ለመውረስ

2ኛ.ለምግበ ሥጋና ለምግበ ነፍስ

3ኛ.ለአንክሮና ለተዘክሮ

ስሙን ለመቀደስና ክብሩን ለመውረስ የተፈጠሩት ሰውና መላእክት ናቸው። ይህ ሲባል እግዚአብሔር ሰውና መላእክትን የፈጠራቸው ክብርና ውዳሴ ሽቶ ነው ማለት አይደለም። እሱ አክብሩኝ አይል ክቡር፣ አወድሱኝ አይል በባሕርይው ምስጉን ነው። አመስግነን የምንጠቀመውና የዘለዓለም ሕይወትና ዕረፍት ባለቤት የምንሆነው እኛ ነን። "እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፍጥረቶቹ ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል እርሱ የተመሰገነ ነው። ለዘለዓለምም ከፍ ከፍ ያለ ነው" (መዝ. ዘሠለስቱ ደቂቅ) የተቀሩት ፍጥረታት ግን በየወገናቸው በልተንና ጠጥተን እንድንጠግብባቸውና እንድንረካባቸው ለምግበ ሥጋ፤ አይተንና ሰምተን እንድንደሰትባቸው ለምግበ ነፍስ፤ የእግዚአብሔርን ጥበብና አፈጣጠር እንድናደንቅባቸውና እንድንሰብክባቸው ለአንክሮና ለተዘክሮ፤ በዚህም ፈጣሪያችንን ለማመስገን ምክንያት እንዲሆኑን ተፈጠሩ።

እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ፍጥረታት መቁጠርና ወስኖ መናገር አይቻልም። እንኳንስ የተለያዩትን ቀርቶ አንዱን ዓይነት እንኳን ብንወስድ ብዙ ዝርያ ስላለው ለቁጥር ይታክታል። "አቤቱ ሥራህ እጅግ ብዙ ነው፤ ሁሉን በጥበብህ አደረግህ" እንዲል ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት (መዝ.103፡24)።

ይሁን እንጂ የሥነ ፍጥረቱን ነገር የሚናገረው አክሲማሮስ የተባለው መጽሐፍ እንደሚያስረዳንና አባቶቻችንም እንዳስተማሩን ብዙውን አንድ እያሉ ቢቆጥሯቸው 22 ፍጥረታት ይሆናሉ። ይህም የ22ቱ አበው ምሳሌ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል "... ከአዳም ጀምሮ እስከ ያዕቆብ ድረስ ያሉ አበው ሃያ ሁለት ናቸው እስከ ሰባተኛይቱ ቀን ድረስ ሃያ ሁለት ፍጥረትን ፈጠረ....."መጽ ኩፋሌ 3፡9/

እነዚህን ሃያ ሁለት ፍጥረታት ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ በቀላሉ ተመልከት/ቺ/

ሰንጠረዥ 1

የሃያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረታት ማሳያ ሰንጠረዥ

ዕለት	የተፈጠሩ ፍጥረታት	አስረጅ	የዕለት ተራ	የዕለቱ ፍጥረታት ብዛት
ዕሁድ	❖ መሬት ❖ ውኃ ❖ ነፋስ ❖ እሳት አራቱ ባሕርያት ❖ ጨለማ ❖ ብርሃን ❖ መላእክት ❖ ሰባቱ ሰማያት ማለትም ጽርሐ አርያም፣ መንበረ መንግሥት፣ ሰማይ ውዱድ፣ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ❖ ኢዮር፣ራማ፣ኤረር	ዘፍ.1፡1-8 ኢሳ.45፡18 ዘዳ.10፡14 ኢሳ.48፡13 1ኛዜና.16፡26 ኢሳ.51፡13 ነህምያ 9፡6 ኢሳ.15፡3 ኢዮ.9፡8 ኤር.15፡3 ኢዮ.37 ኤር.51፡13 መዝ.18፡6 ት.ዘካ.12፡1 መዝ.88፡11 2ኛጴጥ.3፡5 መዝ.101፡25 ኩፋ.2፡4-17 መዝ.135፡5 1ኛመቃ.27፡1 ኢሳ.40፡22 ኢሳ.44፡24	አንደኛ ዕለት ዘፍ.1፡5	8
ሰኞ	በመጀመሪያ ሰዓተ ሌሊት ውኃን ከሦስት ከፈለና አንዱን እጅ በምድር ተወው አንዱን እጅ ከጠፈር በላይ አሰፈረውና ሐኖስ ብሎ ጠራው አንዱን እጅ በመካከል አጽንቶ ጠፈር ካደረገው በኋላ ሰማይ ብሎ ጠራው	ዘፍ. 1፡6-8 ዘፍ.1፡2 1ኛመቃ.27፡3-4	ሁለተኛው ዕለት ዘፍ.1፡8	1

ማክሰኞ	ከሰኞ እስከ ማክሰኞ ውኃና መሬት እንደ አንትና አይብ ተቀላቅለው ነበርና ማክሰኞ ከሌሊቱ በአንድ ሰዓት በምደር ላይ የቀረውን አንዱን እጅ ውኃ ለሦስት ከፈለውና አንዱን እጅ ከመሬት በታች አስፍሮታል ሁለተኛውን እጅ መሬትን እጎድጉዶ ውቅያኖስ አድርጎታል ምድርን የሚከባት ይህ ነው። ሦስተኛውን እጅ ደግሞ በምድር ላይ እንዳለ ባሕር፣ ወንዝ ሐይቅ... እንዲሆን አድርጎታል ከዚህ በኋላ የብስ/ደረቅ/	መዝ.135፡6 ዘፍ.1፡9-13 1ኛመቃ.27፡6-7	ሦስተኛ ዕለት ዘፍ.1፡13	3

	በሆነው ስፍራ በእጅ የሚለቀሙ አትክልትን፣ በማጭድ የሚታጨዱ አዝርዕትን በመጥረቢያ የሚቆረጡ ዕጽዋትን ያለምንም ዘር /እርሻ/ የዕለቱን ፍጥረት ፈጠረ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የማክሰኞ /ምድር/ የምትበላው ለዚህ ነው ይህቺ ምድር ያለ ዘር ፍሬ እንዳስገኘች እሷም ያለዘርዐ ብዕሲ /ያለ ወንድ ዘር/ ጌታችንን ወልዳለችና ነው፡፡			
ረቡዕ	ከእሑድ እስከ ረቡዕ ድረስ ከጠፈር በታች በምድር ላይ ጨለማ እንደመላ ነበር ከማታው አንድ ሰዓት ጀምሮ ሰሌዳውን ከውኃና ከነፋስ አድርጎ ብርሃን በመቀባት በሌሊት ብርሃንን እንዲሰጡና ጠፈርን እንዲያስጌጡ ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብትን ፈጠረ	ዘፍ.1፡14-19 1ኛመቃ.27፡8-9	አራተኛ ዕለት ዘፍ 1፡19	3
ሐሙስ	ከውኃ ውስጥ የተገኙ በደመ ነፍስ ሕይወት ህያዋን የሚሆኑ በልብ የሚሳቡ፣ በእግር የሚሽከረከሩ/ የሚያኮበኩቡ/ በክንፍ የሚበሩ እንስሳትን እራዊትንና አዕዋፍን ፈጠረ	ዘፍ 1፡20-23 1ኛመቃ.27፡10	አምስተኛ ዕለት ዘፈ.1፡23	3
ዓርብ	በዚህ ዕለት ከዕለተ ሐሙስ ከተጠሩት ፍጥረታት ጋር የሚመሳሰሉ ዳሩ ግን ከየብስ /መሬት/ የተገኙ ሦስት ዐይነት ፍጠታትን ፈጥሯል በተጨማሪም አዳምን ተፈጥሯል	ዘፍ.1፡24-31 ዘፈ2፡7 ኩፋ.4፡8 1ኛመቃ.27፡11-14	ስደስተኛ ዕለት ዘፍ.1፡31	4

ቅዳሜ	እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ ከጨረሰ በኋላ ከመፍጠር አረፈ መፍጠር ተወ /ሰንበት አደረገ/	ዘፍ.2፡1-3	ሰባተኛ ዕለት ዘፍ.2፡2	
			ድምር	22

1.11. የፍጥረታት ምሳሌያዊ አስተማሪነት

እግዚአብሔር በአንድም በሌላም ያስተምራል እንዲል /ኢዮ.33፡14/ የእግዚአብሔርን ሀልዎት ብቻ ሳይሆን ባሕርይውንም የሚያስረዱን ቅዱሳት መጻሕፍት እንዳሉልን ሁሉ ፍጥረታቱም ይህንኑ ይተገብራሉ፡፡ በእነዚህ ፍጥረታት ምሥጢረ ሥላሴን፣ ምሥጢረ ሥጋዌን፣ ምስጢረ ትንሣኤ ሙታንን ምሥጢረ ጥምቀትን... ወዘተ አሳምረን መማርና ማጥናት እንችላለን እስኪ ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት፡፡

ሀ. አራቱ ባሕርያት

አራቱ ባሕርያት የምንላቸው እሳት፣ ነፋስ፣ውሃ፣ ምድር /መሬት/ ሲሆኑ እነዚህ ፍጥረታት በመጀመሪያው ቀን በዕለተ ዕሁድ ነው የተፈጠሩት በዓለም ላይ ከተፈጠረው ፍጥረት በሙሉ ከእነዚህ ያልተፈጠረ የለም፡፡ እኒህ ፍጥረታት የተፈጠሩት ‹እምሀበ አልቦ ሀበቦ› ነው ማትም ፈጣሪያችን እግዚብሔር የፈጠራቸው ከሌሉበት ወደሚኖሩበት አምጥቶ ነው፡፡

እነኚህ ፍጥረታት የተፈጠሩበት ዓላማ በፈጣሪያቸው ዘንድ የታወቀ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከማስተሪያነት አነጻር ስናየው ግን ልዑል እግዚብሔር በባሕርይው ያሉትን አራት ነገሮች እንድናውቅ የፈጠራቸው ፍጥረታት ናቸው እግዚአብሔር በባሕርይው አራት ነገሮች አሉት እነርሱም ኃያልነት፣ ፈታሔነት/ፈራጅነት/፣ ባዕልነት/ባለጸጋነት/፣ መንጽሒነት /የሚያነጻ/ ወይም ሩህሩነት እነዚህን በአራቱ ባሕርያት አንጻር አስቀምጠን ስናያቸው፡፡

<u>ኃያልነቱ</u>፡- በእሳት ይመሰላል አሳት ባሕር ገደል ካልከለከለው በስተቀር ቆላውን ደጋውን፣ እርጥቡንና ደረቁን ልብላ ቢል ሁሉ ይቻለዋል እንደዚሁም ሁሉ እግዚብሔር አምላካችን ቸርነቱና ሩህሩነቱ ካልከለከሉት በስተቀር በኃያልነቱ ታላቁንም ታናሹንም ክፉውንም ደጉንም አንድ ጊዜ ላጥፋ ቢል ሁሉ ይቻለዋልና ‹ እግዚአብሔር መኮንነ ጽድቅ ኃያል ለመስተአግሥ ወኢያመጽእ መንሱተ ኩሎ አሚረ፤ እግዚአብሔር እውነት ዳኛ ነው ኃይለኛም ታጋሽም ነው፡፡ ሁልጊዜም አይቆጣም› እንዲል /መዝ.7፡11/

<u>ፈታሒነቱ</u>፡- በነፋስ ይመሰላል ገበሬ የዘራውን እህል ከውድማው ላይ ወቅቶ በመንሹ ባነሳው ጊዜ ነፋሱ ፍሬውን ከገለባው እየለየ ይከምረዋል፡፡ እግዚብሔርም ጻድቃንን ከኃጥአን መናፍቃንን ከምእመናን በቀላሉ ይለያል ‹እረኛም በጎቹን ከፍየሎቹ እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል፡፡› /ማቴ.25፡32/ እንዲል፡፡ ምክንያቱም መንሹ/ሥልጣኑ/ በእጁ ስለሆነ ነው፡፡ ማቴ.32፡12፡፡

ባለጸግነቱ፡- በመሬት ይመሰላል መሬት የምንበላውን የምንጠጣውን ከዚያም ተርፎን የምንለብሰውንና የምናጌጥበትን ሁሉ ታስገኛለች ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔርም ቢሰፍር የማይጎድልበት ቢሰጥ የማያልቅበት ባጸጋ ነው፡፡ ‹... አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና ለሚጠሩትም ሁሉ ባለጠጋ ነው...› ሮሜ 10፡12

መንጽሒነት/ቸርነት/፡- በውኃ ይመሰላል ውኃ ያደፈውን ቢያጥቡበት ያነጻል፣ ያጠራል እግዚአብሔርም አይሠሩ ሥራ ሠርተው አላበጀሁም ማረኝ ይቅር በለኝ ብለው ከተመለሱ ሁሉን ይቀበላል ይምራል፣ ያነጻል፣ ይቀድሳል ውኃን“አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደእኔ ይመጣል ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም”(ዮሐ6፥37)፡፡ ለጥምቀታችን የሰጠንም ለዚሁ ነው፡፡

ለ. <u>የዕለተ ሐሙስ ፍጥረታት</u>

በዕለተ ሐሙስ የተፈጠሩት ሦስት ዓይነት ፍጥረታት ሲሆኑ እነሱም

- በልብ የሚሳቡ
- በእግር የሚያኮበኩቡ /የሚሸከረከሩ/
- በክንፍ የሚበሩ ሁሉም ከባሕር የተገኙ ናቸው (መቃ.ቀዳማዊ 27፡10 ፣ዘፍ.1፡20-23፣ዕዝ.ሱቱ.4፡49-53)፡፡

እነዚህ ፍጥረታት ከባሕር ይፈጠሩ እንጂ በጠባያቸው ለሦስት ተከፍለዋል፡፡ የመጀመሪያዎቹ በዚያው በተፈጠሩበት በባሕር ጸንተው የሚኖሩ ሲሆኑ ሁለተኛዎቹ ከተፈጠሩ በኋላ በረው ከባሕር የወጡና ያልተመለሱ ናቸው ሦስተኛዎቹ ደግሞ አንድ ጊዜ ከባሕር አንድ ጊዜ ከየብስ የሚሉ ናቸው የእነዚህ ምሳሌነትም የምእመናን ሲሆን ባሕር የጥምቀት ምሳሌ ናት እንደተፈጠሩ በባሕር ጸንተው የሚኖሩት በጥምቀታቸው ጽኑአን የሆኑ ምእመናን ምሳሌ ሲሆኑ በረው በረው ከባሕር ወጥተው በዚያው የቀሩት ከተጠመቁ በኋላ በክህደት በኑፋቄ በረው በረው ከቤተክርስቲያን ወጥተው የቀሩትን ምእመናን ይመስላሉ፡፡ አንድ ጊዜ ከባሕር አንድ ጊዜ ከየብስ እያሉ የሚኖሩት አንድ ጊዜ ክርስቲያን ሌላ ጊዜ መናፍቅ አንድ ጊዜ ዘማሪ ሌላ ጊዜ ጨፋሪ አንድ ጊዜ ቤተክርስቲያን ሌላ ጊዜ ጠንቋይ ቤት እያሉ እንደ ፋብሪካ ሰራተኛ በፈረቃ የሚያመልኩ ዘፋኙንም ዘማሪውንም አድናቂህ ነን የሚሉ እንደሰካራም እግር እዚህም እዚያም የሚረግጡ ክርስቲያኖች ምሳሌ ናቸው፡፡

ሌላም ምሳሌነት አላቸው እነዚያ በባሕር ጸንተው የሚኖሩት ፍጠረታት በዚህ ዓለም ኑሮ ጥረው ግረው አርሰው ነግደው ተምረው ተመራምረው ከባለቤታቸው ወልደው አሥራት በኩራት አውጥተው ሥጋውን በልተው ደሙን ጠጥተው ሰንበትን አክብረው በሕገ እግዚአብሔር ጸንተው የሚኖሩ የጻድቃን አምሳል ናቸው፡፡

እነዚያ ከተፈጠሩበት ባሕር በክንፋቸው እየበረሩ የሔዱት ከዘመድ ባዕድ፣ ከአገር ምድረ በዳ ይሻለናል ብለው በረሀ ወርደው ከእንጨት ሥር ከገደል ሥር ወድቀው ጤዛ ልሰው ድንጋይ ተንተርሰው የሚኖሩ የመናንያንና የጻድቃን አምሳል ናቸው /ዕብ.11-37-38/

አንድ ጊዜ ወደ ባሕር አንድ ጊዜ ወደ የብስ ሲመላለሱ የሚኖሩትም የዓለማውያኑ ምሳሌ ናቸው አንድ ጊዜ ወደ ሃይማኖት ሌላ ወደ ክህደት አንድ ጊዜ ወደ ሥርየት ሌላ ጊዜ ወደ ኃጢአት፣ አንድ ጊዜ ወደ ዓለም ሌላ ጊዜ ወደ ገዳም ሲመላለሱ የሚኖሩ ናቸውና /መጽሐፈ አክስማሮስ 2002 ዓ.ም /ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ/ አባ ሠናይ ምስክር /ባሕር ዳር/

1.12 . የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ምንጮች /Sources/

የሃይማኖት ትምህርት እንደ እንግዳ ደራሽ እንድ ውኃ ፈሳሽ ድንገት አይደለም ወይም አንዳንድ የዋሐን እንደሚያስቡት ሃይማኖት በሰዎች ጭነቀትና ፍርሐት / Stress / የተፈጠረ አይደለም። መነሻ ያለው ከጥንት ጀምሮ ምንጩ የሚታወቅ ነው።እነዚህ ምንጮችም ከዚህ እንደሚከተሉት ናቸው።

1ኛ. መጽሐፍ ቅዱስ / Bible /

መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ምን ማለት ነው ተብለህ(ሽ) ብትጠየቅ(ቂ) በአጭሩ እንዲህ ማስረዳት ትችላለህ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ንባብ የሁለት ቃላት ውሑድ ነው መጽሐፍ እና ቅዱስ መጽሐፍ በአንድ ጥራዝ ሥር የተሰበሰበ ጽሑፍ መሆኑ ግልጽ ነው ቅዱስ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ "ክዳሽ" በሱርስት "ጓዲሽ" በግዕዝና በዐረብኛ "ቅዱስ" ካለው ቃል የተገኘ ሲሆን ቀጥታ ትርጉሙም ልዩ፣ ክብር ማለት ነው። ይህ መጽሐፍ ከሌሎች መጽሐፍት ተለይቶ ለምን ቅዱስ እንደባለ ማወቅ ከፈለክ(ግሽ) መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርትን መከታተል ይኖርብሃል(ሻ።)

ለምሳሌ

- "በኋለኞች ዘመናትአንዳንዶች የሚያስቱመናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ"1ኛ.ጢሞ.4÷1-2 የሚለውን ስታነብ(ቢ) ቅድስት ቤተ ክርስትያን የምታስተምረው የጥብቅና እና የጥበቃ ትምህርት ነው ትዝ የሚልህ።
- "እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ" ዘፍ.1÷1 የሚለው ቃል የሥነ ፍጥረት ባለቤት እግዚአብሔር ነው ለሚለው ትምህርታችን ዋና ማስረጃ ነው።

- "ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው የመላለሳሉና፣ብዙ ጊዜ ስለእነሱ አልኋችሁ አሁንም እነኳእያለቀስሁ እላለሁ። መጨረሻቸው ጥፋት ነው።ሆዳቸው አምላካቸው ነው። ክብራቸው በነውራቸው ነው። አሳባቸው ምድራዊ ነው" /ፊሊ.3÷18/

ስለሆነም ከዚህ ቅዱስ መጽሐፍ ውጪ በቀዳሚነት የትምህርተ ሃይማኖት ምንጭ ሊሆን የሚችል ሌላ መጽሐፍ የለም። እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በዚህ መልኩ ብንተነትነው በትምህርተ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያናችን ለምተሰጠው አስተምህሮ መነሻና መሠረት ሆኖ ነው የምናገኘው።

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የሃይማኖት መጀመሪያ ባይሆንም ትምህርተ ሃይማኖትን ማስተማሪያና መመሪያ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀድሞ ከፍጥረቱ /ሕዝቡ/ ጋር ያለ መጽሐፍ ቃል በቃል ይነጋገር ነበርና ነው።

2ኛ. ትውፊት / Holy Tradition /

ትውፊት " አወፈየ" አቀበለ አወረሰ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ቅብብል፣ ርክክብ፣ ውርስ ማለት ነው መንፈሳዊ ትውፊት ከቀደሙት አባቶቻችንና እናቶቻችን፤ በዘመነ ክርስትና ደግሞ ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ እምነታቸውን፣ ምግባራቸውን፣ በግላቸው ያካበቱትን የሃይማኖት ጽናትና የሥራ ፍሬያቸውን፣ በመከራ ጊዜ ጥንካሬያቸውን በደስታ ጊዜ ትዕግስታቸውን፣ ፍቅራቸውንና አንድነታቸውን ወዘተ.. የምንወርስበትና ተረክበን የምናስረክብበት እውነታ ነው።

ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈ በኋላ ብቻም ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊትም ነበረ ምክንያቱም የሰውና የእግዚአብሔር ግንኙነት የጀመረው ከዛ በፊት ስለሆነ ነው ይልቁንም ራሱ መጽሐፍ ቅዱስን ከጥፋት የታደገውና ለትውልዱ ሰፍሮና ቆጥሮ ያስረከበው ትውፊት ነው።

ያለ ትወፊት ይህ መጽሐፍ ቅዱስ በትክክልም የእግዚአብሔር ቃል ነው ብሎ ቆጥሮና አረጋግጦ የተቀበለ በዚህ ዘመን የታለ) እኛ ግን በረከታቸው ይድረሰንና ቅዱሳን አባቶቻችን በተለይም 318ቱ ሊቃውንት የተበተነውን ሰብስበው እውነተኛውን ከሐሰተኛው ለይተው ርዕስ፣ ምዕራፍና ቁጥር ሰጥተው የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አረጋግጠው እንደሰጡን በመንፈሳዊ ትውፊት እንረዳለን ይህንንም እናምናለን።

ስለዚህ ትውፊት በቅብብል የመጣ፣ የወረደ፣ የተወረሰ የትምህርተ ሃይማኖት አንደኛው ክፍል ነው / one of the Surses of doctrine / "ባፍም በመጣፍም" የሚለው

አባባላችን /መጽሐፍ ቅዱስንና ትውፊትን /ለትምህርተ ሃይማኖት በምንጭነት መጠቀማችንን የሚጠቁም ነው። ስለዚህ እኛ ባፍም በመጣፍም / በመጽሐፍ ቅዱስና በትውፊት / ማለትም / Holy Tradition/ የተላለፈ ሃይማኖት ነው ያለን። ያለ ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስማ ቢሆን ሙሉ አይደለም

ለምሳሌ

- ሙሴ እስራልን ለማውጣት በተላከ ጊዜ".....ጌታ ሆይ እኔ አፌ ኮልታፋ ምላሴም ፀያፍ የሆንሁ ሰው ነኝ" ብሎ ነበር። ሙሴ አንደበቱ ኮልታፋ የሆነበት ምክንያት በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ አናገኘውም ዳሩ ግን በትውፊት የተገኘው በሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ ነው የምናገኘው።
- በሉቃስ ወንጌል እንደምናነበው ጌታን በቤተ መቅደስ የታቀፈው አረጋዊው ስምዖን"ጌታ ሆይ አሁን እንደቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ" ሲለው ምን ማለቱ ነው። ለምንድን ነው ስንብት የጠየቀው? ይሄ ያለትውፊት ግልጽ አይሆንም። በመሆኑም ትውፊት ከመጽሐፍ ቅዱስ ባልተናነሰ መልኩ ለትምህርተ ሃይማኖት ዋና ተጠቃሽ ምንጭ ነው።

በኦርቶዶክሳውያን አስተምህሮ ትውፊት አፈ ታሪክ / Legand / አይደለም በምእመናን ላይ አድሮ የሚኖር የመንፈስ ቅዱስ የማያቋርጥ የዕለት ተዕለት ሥራ ነው። በመሆኑም መንፈሳዊ ትውፊት የማይንቀሳቀስ ግን የማይሞት ሕያው የሆነ /Not static but dynamic / ምንጭ ነው። በሌላ መልኩ ካየነው መንፈሳዊ ትውፊት የመንፈስ ቅዱስ ሕያው ምስክርነት ነው ምክንያቱም በመንፈሳዊ ትውፊት የሚታሰቡትና የሚወረሱት ተግባራት ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ጥበባት ስለሆኑ ነው። " የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል" እንዲል /ዮሐ.15፡26 ,16፡13/

መንፈሳዊ ትውፊት በቤተክርስቲያን የሚጠበቅ በቻ ሳይሆን ሕያው ሆኖ የሚኖርም ነው። / Tradition is not only kept by the church it Lives in the church (RF1Timothy wore the orthodox church condon 1964,p.203-215 / ስለዚህ በቅድስት ቤተክርስቲያን እስከኖርን ድረስ መንፈሳዊ ትውፊትን መቀበል ግድ ይለናል። አንዱ የትምህርተ ሃይማኖታችን ምንጭ እሱ ነውና ዳሩ ግን ማንኛውንም ትውፊት ቤተክርስቲያናችን የምትቀበለው መጽሐፍ ቅዱስን ማዕከል ሲያደርግ ብቻ ነው።

3ኛ. ትምህርተ አበው

የቅዱሳን አባቶቻችን ትምህርት ሌላውና ተዓማኒ የነገረ ሃይማኖት ትምህርታችን ምንጭ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ የሃይማኖት አባቶቻችንን እንድንሰማ ያዘናል " የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፤ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው" እንዲል /ዕብ.13፡7/ ስለዚህ በትምህርተ ሃየሚኖት ትምህርተ አበው /የአባቶች አስተምህሮ/ እጅግ በጣም ወሳኝ ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር የአባቶቻችን አምላክ ስለሆነ። " የአባቶችህ አምላክ እግዚአብሔር እኔ ነኝ" ይለናል /ዘፍ.46፡3/

በቤተክርስቲያናችን ሥርዓተ ትምህርት አበው የምንላቸውን በጥቅሉ ስናስቀምጣቸው ቅድመ ልደተ ክርስቶስና ድኅረ ልደተ ክርስቶስ ብለን በሁለተ ከፍለን ማየት እንችላለን። ይህማ ማለት በብሉይ ኪዳን ያሉት እንዳሉ ሆነው በሐዲስ ኪዳን ሐዋርያት፣ ሐዋርያነ አበው፣ ሊቀውንተ ቤተክርስቲያን ተብለው ይጠራሉ።

ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ማርያም ተገልጦ በዚህች ምድር ሲያስተምር በነበረበት ጊዜ ከዋለበት እየዋሉ ካደረበት እያደሩ የቃሉን ትምህርት የእጆቹን ተዓምራት ሲሰሙና ሲያዩ የነበሩቱ ሐዋርያት ሲባሉ፤ እርሱ በክብር ካረገ በኋላ ከሐዋርያቱ እግር ሥር ቁጭ ብለው የተማሩና የአባቶቻቸው የሐዋርያትን ቃል በቀጥታ የሰሙ ገቢረ ተአምራታቸውንም ያዩና የተረዱ የቅድስና መዓዛቸውን ያሸተቱና ቅዱስ አካላቸውን የነኩቱ ሐዋርያነ አበው ይባላሉ። ከእነሱ በመቀጠል አሁን እስካለችው ቤተክርስቲያን ያሉቱ ደግሞ ሊቀውንተ ቤተክርስቲያን ተብለው ይጠራሉ ትምህርተ አበው ስንልም የእነዚህን ሁሉ ትምህርት ማለታችን ነው።

የእነዚህ አባቶቻችን በመጽሐፍ ያለ ትምህርታቸው በትውፊት የወረስነው የቅድስና ኑሮአቸው ሁሉ አማናዊ የሃይማኖት ትምህርታችን ምንጭ ነው። ማለት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሚወደውና ለመንፈስ ቅዱስ ልጁ ለጢሞቴዎስ "አንተ ግን ትምህርቴን አካሔዴን አሳቤንም እምነቴንም፣ ትዕግሥቴንም፣ ፍቅሬንም፣ መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተልህ" በማለት በትክክለኛው መስመር ላይ መቆሙን እንደመሰከረለት እኛም እንደ ጢሞቴዎስ ሁሉ የአባቶቻችንን ትምህርት እካሔድ፣ አሳብ፣ እምነት፣ትዕግስት፣ፍቅር፣ ጽናት፣ስደትና መከራ በአጠቃላይ የሃይማኖት ጽናትና የምግባር ትጋት ስናጠና በትክክለኛው መስመር ላይ መቆማችን ይሰማናል ከምንጩ እየቀዳን መሆኑንም እናረጋግጣለን/2ኛጢሞ3፡10

ማጠቃለያ፡

የትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ የመጀመሪያው ምዕራፍ ከሙሉ በከፊሉ ከረዥሙ ባጭሩ ደረሰ ተፈጸመ፡፡ ይህ ማለት ውቅያኖስ ከሆነው የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እንደመጨለፍ ያለ ነው፡፡ በዚህ ክፍል የሰፈረው ዝርዝር ንባብ የሚያስረዳው በዋነኛነት ሁለት መሠረታዊ አሳቦችን ነው፡፡ እነሱም አንደኛው የሃይማኖትን ምንነት እንዲሁም የእግዚአብሔርን ህልውትና ባሕሪይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሃይማኖት የምናመልከው እግዚአብሔር መኖሩ ከሚታወቅባቸው መገለጫዎች አንዱና ዋነኛው ስለሆኑት ፍጥረታትና አፈጣጠራቸው ነው፡፡

ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኒቱ ጥሪ እንዲደርስህ(ሽ) ሰማያዊ የሆነው በጎ የዕውቀት መዓዛዋ እንዲሸትህ(ሽ) ያደርጋል፡፡ ዳሩ ግን መዓዛቸው ሌላ ትምህርታቸው ኑፋቄ የሆነ፤ መምህራን ሳይሆኑ መምህራን ነን ብለው በድፍረት ራሳቸውን ያሰማሩ ብዙዎች አሉና ይህንን ትክክለኛ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በጎ መዓዛ (ሽታ) ይዘህ(ሽ) መጠጋት ያለብህ(ሽ) ወደ ትክክለኞቹ የቤተ ክርስቲያን መምህራን ነው፡፡ ይንን ጉዳይ አስመልክተው የጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ነበሩት አቡነ መቃርዮስ እንዲህ መክረው ነበር፡፡

"እሸትን ከእሸት መርጦ እንዲበሉ ሃይማኖትንም ሲማሩ ከሰው ሰው መርጦ ደግ ምግባርና የቀና ሃይማኖት ካለው ሰው መማር ይገባል፡፡ ሃይማኖት ከሌለው ግን መማር አይገባም ይጠበቋል እንጂ፡፡ መናፍቃን ሲሆኑ ሃይማኖታውያን መስለው፤ሐሰተኞች ሲሆኑ እውነተኞች መስለው፤ሥጋውያን ሲሆኑ መንፈሳውያን መስለው፤ከሚመጡ ሐሰተኞች መምህራን ተጠበቁ፡፡ ውስጣቸውን ቢመረምሯቸው ግን ሰውን እየነጠቁ ወደ ክህደት፣ወደ ገሃነም እሳት የሚያገቡና ወርውረው የሚጥሉ ናቸው፡፡ እንዲል ማቴ.7÷15" ብፀዕ አብነ መቃርዮስ፣(መንገደ ሰማይ)

አሁን ንባብህን(ሽን) ከጨረስክ(ሽ)፣አልገቡኝም የምትላቸውን(ትያቸውን) ጠይቀህ(ሽ) ከተረዳህ(ሽ)፣ተጨማሪ መጻሕፍትን በመመልከት በያዝከው(ሽው) ላይ ከጨመርክ(ሽ) ወደመጀመሪያው ገጽ ተመለስና(ሺና) ትጠብቃቸው(ቂያቸው) የነበሩ ብቃቶችን አግኝተህ(ሽ) እንደሆነ ራስህን(ሽ) ጠይቅ(ቂ)፡፡ ከዛም ወደ ምዕራፍ ሁለት እለፍ(ፊ)

ዋቢ መጻሕፍት (Biblography)

- መጽሐፍ ቅዱስ፣በአማርኛ ብሉይና ሐዲስ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ፣1980 ዓ/ም፡፡

- The Holy Bible, London, The British and foreign Bible Society Great Britain, Combridge university press.
- ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ፣ ፍኖተ አዕምሮ ፣1953 ዓ.ም።
- The Ethiopian Orthodox Church (EOTC) Taithe and Order, The Enterthronenent of the Third palriarch, Addis Ababa ፣1968.
- ፍኖተ ሕይወት ፣አባ ማትያስ የካናዳ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፣(ዓ.ም የለውም)።
- ፍኖተ እግዚአብሔር፣ብፁዕ አቡነ ቶማስ ሊቀ ጳጳስ፣የካቲት ፣1990 ዓ.ም።
- መሠረተ ሃይማኖት፣ሊቀ ትጉሃን ኃ/ጊዮርጊስ ዳኘ፣ 2004 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ምሥጢር፣አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የደረሰውና መ/ር ኃ/ማርያም ላቀው የተረጎመው ፣2000 ዓ.ም።
- ቅዳሴ ማርያም አንድምታ (ትርጓሜ)፣ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ 1983 ዓ.ም።
- መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን፣ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት (ያልታተመጥራዝ፣1988ዓ.ም።
- ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት፣ማኅበረ ቅዱሳን ፣መስከረም 1993 ዓ.ም።
- ወንጌል ቅዱስ ትርጓሜ፣ተስፋ ገብረ ሥላሴ የታተመ፣1985 ዓ.ም።
- የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ዓምደ ሃይማኖት ሰንበት ትምህርት ቤት ያልታተመ የማስተማሪያ ደብተር
- ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ፣ፍልስምና (አምላክ ፣ሰውና ኃይማኖት) ፪፣ 2004 ዓ.ም።
- ” ” ” ” ” (ፖለቲካ ሥነ ከዋክብት ገዳ እምነት የለሽ...) ፫፣ሐምሌ2005 ዓ.ም።
- ሐመረ ተዋሕዶ (የሐመር መጽሔት ልዩ ዕትም መጽሐፍ)፣ ነሐሴ 2001 ዓ.ም።
- Doctrion of Man (Father Jocy), ያልታተመ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ማስተማሪያ “ሞጁል”፣ 2006 ዓ.ም።
- መልአከ ሰላም አድማሱ ጀንበሬ (ኰኵሐ ሃይማኖት)፣1989 ዓ.ም.፣ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ አዲስ አበባ
- ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው፣1990ዓ.ም. አዲስ አበባ፣ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት
- ደስታ ተክለ ወልድ፣1948 ዓ.ም.(መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ) አርቲስቲክ ማተሚያ አዲስ አበባ
- አክሲማሮስ